# የአዲስ አበባ ከተማ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን

# የትራፊክ ቁጥጥር እና ቅጣት አፈፃፀም አሰራር
# የተሻሻለ ማንዋል

መጋ ቢት 2018 ዓ .ም
አ ዲ ስ አ በ ባ

ማውጫ

ክፍል አንድ ....... 7

1. መግቢያ ....... 7

1.1 ትርጓሜ ....... 8

1.2 የተፈፃሚነት ወሰን ....... 9

1.3 የባለስልጣኑ ራዕይ ....... 9

1.4 የባለስልጣኑ ተልዕኮ ....... 9

1.5 የባለስልጣኑ እሴቶች ....... 10

1.6 ዓላማ ....... 10

1.6.1 ዝርዝር ዓላማዎች ....... 10

1.7 ግብ ....... 11

ክፍል ሁለት ....... 12

2. የባለስልጣኑ መዋቅራዊ አደረጃጀትና የቁጥጥር ክፍሉ ተግባራት ....... 12

2.1 የባለስልጣኑ መዋቅራዊ አደረጃጀት ....... 12

2.2 የባለስልጣኑ ስልጣንና ተግባራት ....... 12

2.3 የትራፊክ ቁጥጥር፣ ኩነት አስተዳደር እና መድን ፈንድ ዳይሬክቶሬት ተግባር እና ኃላፊነት ....... 16

2.4 የትራፊክ ቁጥጥር ቡድን መሪ ተግባራት ....... 16

2.5 የመንገድ ትራፊክ ቁጥጥር ቡድን አስተባባሪ ....... 17

2.6 የትራፊክ ቁጥጥር ሽፍት ሱፐርቫይዘር ....... 18

2.7 ከፍተኛ የትራፊክ ተቆጣጣሪ ....... 18

2.8 ሲስተም ባለሙያ ....... 20

2.9 የማዕከል ትራፊክ ቁጥጥር ቡድን ተግባራት ....... 20

2.10 የትራፊክ ቁጥጥር ባለድርሻ አካላት እና ፍላጎታቸው ..... 21

ክፍል ሶስት ..... 25

3. የትራፊክ ቁጥጥር ስራ አጠቃላይ መርሆዎች ..... 25

3.1 ህግና ስርዓትን የመከተል መርህ ..... 25

3.2 ሰብአዊ ክብርን የመጠበቅና ከአድሎ የፀዳ መሆን ..... 25

3.3 በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነትን ማረጋገጥ ..... 26

3.4 ቴክኖሎጅ የተደገፈ አገልግሎት መስጠት ..... 26

ክፍል አራት ..... 27

4. የትራፊክ ቁጥጥር አሰራር፣ የግብዓት አጠቃቀም እና የዲሲፕሊን ሁኔታ ..... 27

4.1 የትራፊክ ቁጥጥር የአሰራር ማንዋሉ ዝግጅትና ይዘት ..... 27

4.2 የትራፊክ ቁጥጥር የስራ ክፍል አደረጃጀት ..... 27

4.3 የትራፊክ ቁጥጥር መጀመሪያና መጨረሻ ..... 28

4.4 ለትራፊክ ቁጥጥር ስራ ትኩረት የሚደረግባቸው ቦታዎች ..... 28

4.5 ለትራፊክ አደጋ አጋላጭ መንስኤ (Risk Factors) በሆኑ የጥፋት አይነቶች ..... 28

4.6 በዋና ዋና እና መጋቢ መንገዶች እንዲሁም መጋጠሚያዎች አካባቢ ..... 28

4.7 የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጡ ተርሚናሎችና መጫኛና ማውረጃ(ቤይ) ያለባቸው አካባቢዎች ..... 29

4.8 በሰዓት የተገደቡ የመንገድ ምልክትና ማመላከቻዎች የተቀመጡበት አካባቢ ..... 29

4.9 ለአውቶብስ ብቻ የተለዩ መስመሮችን ማስከበር ..... 29

4.10 ትምህርትቤቶች እና የኮንስትራክሽን ስራ በሚገኙባቸው አካባቢዎች ..... 30

4.11 እግረኞች የሚበዙባቸው አካባቢዎች ..... 30

4.12 ከፍጥነት ወሰን በላይ ማሽከርከር እና አልኮል ጠጥቶ ማሽከርከር ቁጥጥር የሚካሄድባቸው ቦታዎች ..... 30

4.13 የትራፊክ ቁጥጥር የሚካሄድባቸው ቀናትና ሰዓቶች ..... 31

4.13.1 የትራፊክ ቁጥጥር የሚካሄድባቸው ቀናቶች ..... 31



Addis Ababa Traffic Management Authority

4.13.2 የትራፊክ ቁጥጥር የሚካሄድባቸው ሠዓቶች ..... 31

4.13.3 የትርፍ ሰዓት ስራን በተመለከተ ..... 31

4.14 የትራፊክ ቁጥጥር የሚካሄድባቸው አካላት ..... 32

4.15 የትራፊክ ቁጥጥር የስራ ቦታ እና ፈረቃ ..... 32

4.16 በመንገድ ትራንስፖርት ህግ ተላላፊዎች ላይ እርምጃ ስለመውሰድ ..... 32

4.17 የተሽከርካሪ ሰሌዳ ስለመፍታት ..... 33

4.18 የቅጣት አዘገጃጀት ..... 33

4.19 የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ ስለሚመለስበት ሁኔታ ..... 34

4.20 ለደንብ ተላላፊዎች በቂ መረጃ ስለመስጠት ..... 35

4.21 የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ ስለማስረከብ ..... 35

4.22 የስራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ..... 36

4.23 በቁጥጥር ወቅት ተገቢውን ጥንቃቄ ስለማድረግ ..... 36

4.24 የትራፊክ ቁጥጥር ስራን ባሰናከሉ ደንብ ተላላፊዎች የሚጣል ቅጣት ..... 36

4.25 የትራፊክ አደጋ ሁኔታ አመዘጋገብ ..... 36

4.26 የትራፊክ ፍሰትን የማስተናበር ስራ ..... 37

4.27 የስራ ቁሳቁሶች እና ከህግ ተላላፊዎች የተረከቡዋቸውን መረጃዎች በአግባቡ ስለመያዝ ..... 37

4.27.1 የትራፊክ ቁጥጥር ቁሳቁሶች አያያዝና አጠቃቀም ..... 38

4.27.2 የትራፊክ ቁጥጥር የደንብ ልብስ አጠቃቀም ..... 38

4.27.3 የሞተር ብስክሌት አጠቃቀም ..... 39

4.28 ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን ቅንጅታዊ የትራፊክ ቁጥጥር ማድረግ ..... 39

4.28.1 ከአጎራባች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ከማዕከል ትራፊክ ቁጥጥር ጋር በመሆን ቁጥጥር ማድረግ ..... 39

4.28.2 ከአዲስ አበባ ከተማ ትራፊክ ፖሊስ ጋር በመሆን ቅንጅታዊ የስምሪት ቁጥጥር ማድረግ ..... 39

4.28.3 ከአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ባለስልጣን ጋር በመሆን ቅንጅታዊ የትራፊክ ቁጥጥር ማድረግ ..... 40

4.28.4 ከትራንስፖርት ቢሮ ስምሪት ቁጥጥር ጋር በቅንጅት ቁጥጥር ማድረግ .....40

4.28.5 ከአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ጋር በቅንጅት መስራት .....40

ክፍል አምስት .....41

5. የዲጅታል የትራፊክ ቅጣት ማስፈፀሚያ ሲስተም አሰራር .....41

5.1 ቅጣት በዲጅታል የትራፊክ ቅጣት ማስፈፀሚያ ሲስተም ብቻ ስለማስፈጸም .....41

5.2 የትራፊክ ቅጣት ማስፈፀሚያ ሲስተም አጠቃቀም .....41

5.3 ልዩ ሁኔታ .....42

5.4 በትራፊክ ተቆጣጣሪ የተፈጸመ ስህተት ስለሚታረምበት ሁኔታ .....43

5.5 የትራፊክ ግጭት/ክስተት መረጃ አያያዝ .....43

5.6 ተፈላጊ ተሽከርካሪ ስለመመዝገብ .....43

5.7 በስህተት ወደ ባለስልጣኑ ሂሳብ ገቢ የተደረገ ገንዘብ ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ .....44

5.8 ቅጣት ወይም የተመዘገበ የነጥብ ሪከርድ ከሲስተም ሊሰረዝ የሚችልባቸው ሁኔታዎች .....44

5.9 የማዕከል ሲስተም አድሚንስትሬተር ኃላፊነት .....45

5.10 የትራፊክ ቁጥጥር እና ኩነት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ኃላፊነት .....45

5.11 የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊነት .....46

5.12 የቅርንጫፍ ሲስተም አድሚንስትሬተር ኃላፊነት .....46

5.13 የትራፊክ ተቆጣጣሪ ኃላፊነት .....47

ክፍል ስድስት .....48

6. የጥፋት ሪከርድ ስለሚያዝበት ሁኔታ እና የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ስለማገድ .....48

6.1 የጥፋት ሪከርድ ስለመያዝ .....48

6.2 የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ስለማገድ .....48

6.3 የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እገዳ አፈፃፀም .....49

6.4 የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እገዳ መቆጠር የሚጀምርበት ጊዜ .....50

6.5 የእውቀትና ክህሎት ስልጠና ስለመውሰድ ........ 51

6.6 የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እገዳ ጊዜያቸውን ስላጠናቀቁ አሽከርካሪዎች ........ 51

6.7 የእገዳ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሊመለስ ስለሚችልባቸው ሁኔታዎች ........ 52

6.8 ከእግድ ነፃ ማስረጃ ስለመስጠት ........ 52

6.9 የትራፊክ ቅጣት ሪከርድ ማስረጃ ስለመስጠት ........ 53

6.10 የይርጋ ጊዜ ........ 53

ክፍል ሰባት ........ 54

7. የቁጥጥር መረጃዎች አያያዝ፣ ሪፖርት እና ቅሬታ አቀራረብ ስነ ስርዓት ........ 54

7.1 መረጃ አያያዝ ........ 54

7.2 ሪፖርት ስለማቅረብ ........ 54

7.3 የድጋፍና ክትትል ግምገማና ግብረ መልስ አሰጣጥ ........ 54

7.3.1 ድጋፍና ክትትል ........ 54

7.3.2 የግምገማና ግበረ መልስ አሰጣጥ ሂደት ........ 54

7.3.3 የቅሬታ አቀራረብ ስነ ስርዓት ........ 55

7.4 የዚህ ማንዋል አካል ስለሚሆኑ ሰነዶች ........ 55

7.5 በኃላፊነት ስለመጠየቅ ........ 55

7.6 የአሰራር ማንዋሉ ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ........ 55

7.7 የአሰራር ማንዋሉ በስራ ላይ የሚውልበት ጊዜ ........ 55

ለትራፊክ ተቆጣጣሪ ባለመታዘዝ የሄዱ አሽከርካሪዎች መመዝገቢያ ቅፅ ........ 57

የቅጣት ፓድ ያልተዘጋጀላቸው የቅጣት አይነቶች መቅጫ ቅፅ ........ 58

የትራፊክ ህግ ተላላፊዎች የአድራሻ ማሳወቂያ ቅፅ ........ 60

የትራፊክ ህግ ተላላፊዎች ቅሬታ ማቅረቢያ ቅፅ ........ 61

የዲስፐሊን እርምጃ እንዲወሰድ በትራፊክ ተቆጣጣሪው የሚቀርብ አቤቱታ ማቅረቢያ ቅፅ ........ 62

## ክፍል አንድ

### 1. መግቢያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን በማሻሻል በዜጎች ላይ እየደረሰ ያለውን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ እና ሰላማዊና ተቀባይነት ያለው የትራፊክ ፍሰት እንዲኖር ለማድረግ ተቋቁሞ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ የትራፊክ አደጋንም ሆነ የትራፊክ መጨናነቅን ትርጉም ባለው መልኩ ለመቀነስ የትራፊክ ቁጥጥር ስራን ማጠናከር ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡

ባለስልጣኑ እያከናወናቸው የሚገኙ ተግባራት የሰውን ህይወት ከመታደግ አንፃር በፍጥነት እያደገ የነበረውን የከተማው የሞት መጠን እንዲቀንስ አስችሏል፡፡ ይሁን እንጅ በከተማችን ውስጥ የተመዘገበውን ውጤት ለማስቀጠልና ተጨማሪ ውጤቶችን ለማስመዝገብ የተጀመሩ ስራዎችን አጠናክሮ መቀጠል፣ነባር አሰራሮች በየጊዜው እየፈተሹ ማስተካከል እና አዳዲስ አሰራሮችን በጥናት በመለየት በመተግበር መረባረብ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ በባለስልጣኑ ስር ባሉ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ቁጥራቸው ከፍ ያለ መንገድ ትራፊክ ተቆጣጣሪ ሠራተኞች በመመደብ እንዲሰሩ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጅ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ስር የሚገኙ የትራፊክ ቁጥጥር ሠራተኞች ስምሪት ወጥነት ያለው ባለመሆኑ የሁሉንም ቅ/ጽ/ቤቶች ውጤታማነት በመገምገምና በመደገፍ አፈፃፀማቸውን በመከታተል በመመዘ እንዲሁም ለቁጥጥር ስራው የሚያስፈልግን ግብዓት አጠቃቀምን ከተጨባጭ ሁኔታው አንፃር መመዘን እና ተገቢ ድጋፍ ማድረግ አልተቻለም፡፡ በተለይም በስራ ላይ እያጋጠሙ የሚገኙ ችግሮችን ወጥነት ባለው መልኩ ደረጃ በደረጃ ለመፍታት የሚያስችል መዋቅራዊ አደረጀጀት ተፈጥሮ ተግባራዊ ካለመደተረጉም በተጨማሪ የትራፊክ ቁጥጥር ተግባሩን በሚፈለገው ደረጃ መምራት አልተቻለም፡፡

በሌላ በኩል ባለስልጣኑ በከተማ ደረጃ በሪፎርም ካለፉ ተቋማት መካከል አንዱ እንደመሆኑ መጠን አዲስ የሪፎርም ትግበራ በማከናወን አጠናቆ ወደስራ በመግባቱ ሪፎርሙን ውጤታማ ከሚያደርጉ መንገዶች አንዱ በተቋም ደረጃ የሚሰጠው አገልግሎት በቴክኖሎጅ የታገዘ እንዲሆን ማድረግን የሚጨምር በመሆኑ የትራፊክ ቁጥጥር ስራውን ለማዘመን የሚያስችል አውቶማቲክ የትራፊክ ቅጣት ማስፈፀሚያ ሲስተም በማልማት ወደስራ እንዲገባ የተደረገ ሲሆን የሲስተሙ ትግበራ የሚመራበት አሰራር መዘርጋት አስፋለጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 557/2016 አንቀጽ 95 ንዒስ አንቀጽ 12 መሠረት በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል በማንኛውም ጊዜ የኤሌክትሮኒክስ ቴክኖሎጅ ቁጥጥር እና የትኬት መመዝገቢያ ስርዓቶችን በመከተል ወይም ተግባራዊ በማድረግ የደንቡን ድንጋጌዎች የተላለፉትን አሽከርካሪዎች መቆጣጠርና መቅጣት እንዳለበት የሚደነግግ በመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሠራተኞች አዋጅን፣ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብን፣ የትራፊክ ቅጣት አፈፃፀም እና ቁጥጥር ሠራተኞች የስነ ምግባር መመሪያ እንዲሁም የተቋሙን መዋቅራዊ አደረጃጀት ሰነድ መነሻ በማድረግ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀጽ 54 መሠረት በተሰጠዉ ስልጣን መሠረት ይህን አሰራር ማኑዋል አውጥቷል፡፡

## 1.1 አጭር ርዕስ

ይህ የአሰራር ማንዋል "**የትራፊክ ቁጥጥር እና ቅጣት አፈፃፀም አሰራር የተሻሻለ ማንዋል**" ተብሎ ሊጠቀስ/ሊጠራ ይችላል፡፡

## 1.2 ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ነው፡፡
2. **"ባለስልጣን"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማንጅመንት ባለስልጣን ነው፡፡
3. **"የባለስልጣኑ የበላይ አመራር"** ማለት የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ማለት ነው፡፡
4. **"አሽተሽ"** ማለት አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪ ፣ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፡፡
5. **"ቅርንጫፍ ጽ/ቤት"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን ስር በተዋረድ የተቋቋሙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ናቸው፡፡
6. **"ስራ አስኪያጅ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ስራ አስኪጆች ናቸው፡፡
7. **"የትራፊክ ተቆጣጣሪ መስሪያቤቶች"** ማለት አግባብ ባለው ህግ መሠረት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህጎችን ለማስከበር ስልጣን የተሰጣቸው ተቋማት ነው፡፡
8. **"ትራፊክ"** ማለት በማንኛውም መንገድ አንድ ወይም ብዙ ሆነው የሚተላለፉ እግረኞች ወይም ሰው ተቀምጦባቸው ወይም እየተነዱ ወይም እየተጠበቁ የሚሄዱ እንስሶችና ተሽከርካሪዎች ናቸው፡፡
9. **"ትራፊክ ተቆጣጣሪ"** ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ህጎች መከበራቸውን ለመቆጣጠር እና የትራፊክ ፍሰትን ለማስተናበር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን ተቀጥረው የተሰማሩ የቁጥጥር ሠራተኞች ናቸው፡፡
10. **"ትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ"** ማለት አግባብ ባለው ህግ መሠረት የትራፊክ ህጎች መከበራቸውን ለመቆጣጠር እና የትራፊክ ፍሰትን ለማስተናበር አግባብነት ባለው ሕግ ሥልጣን የተሰጠው የፖሊስ አባል ነው"፡፡
11. **"የጥፋት ሪከርድ"** ማለት በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 557/2016 መሠረት በትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች ላይ በጥፋት ላይ በመመስረት የሚመዘገብ ነጥብ ነው፡፡
12. **"ፈቃድ"** ማለት አስቀድመው በነበሩ ህጎችም ሆነ በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 መሠረት የተሰጠ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ነው፡፡
13. **"ፈቃድ ሰጪ አካል" ማለት** አግባብ ባለው ህግ መሠረት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የመስጠትና የማደስ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ናቸው፡፡

14. **"የህክምና ማስረጃ"** ማለት ህጋዊ እውቅና ባለው የህክምና ተቋም በጠቅላላ ሀኪም ደረጃ የተሰጠ የትራፊክ አደጋ ተጎጅውን የጉዳት መጠን ወይም ሞት የሚገልፅ የሰነድ ማስረጃ ነው፡፡
15. **ዲጅታል የትራፊክ ቁጥጥር እና የትራፊክ ቅጣት ማስፈጸሚያ ስርዓት ማለት** በመንገድ ትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች ላይ የሚከናወን የቁጥጥር ስራ እና የሚጣለው ቅጣት በዲጅታል መልክ እንዲተላለፍ በማድረግ ደንብ ተላላፊው መረጃዎች መዝግቦ በመያዝ ቅጣቱን እንዲፈጽም የሚደረግበት የኤሌክትሮኒክስ ስርዓት ነው፡፡
16. **"ቅጣት"** ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ በመተላለፍ በተቆጣጣሪው አካል የሚወሰድ እርምጃ ነው፡፡
17. **"ስምሪት"** ማለት የትራፊክ ቁጥጥር ባለሙያ የትራፊክ ቁጥጥር ስራ እንዲያከናውን በስራ ክፍሉ የሚሰጥ ድልድል ነው፡፡
18. **"ፈረቃ"** ማለት የትራፊክ ቁጥጥር ባለሙያዎች ተግባራቸውን የሚያከናውኑበት በየጊዜው የሚቀያየር በስራ ክፍሉ የሚደለደል የስራ መርሀ ግብር ወይም ሰዓት ነው፡፡
19. **"አሽከርካሪ"** ማለት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለው ሰው ነው፡፡
20. **"የቅጣት አፈፃፀም"** ማለት የትራፊክ ህግ ተላላፊዎች ላይ በትራፊክ ተቆጣጣሪ የቅጣት ወረቀት/በታብሌት ጽፎ ከመስጠት ጀምሮ ቅጣት ከፍሎ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድን ወይም ሰሌዳን እስከመረከብ እንዲሁም የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እስከማገድ ያለውን ሂደት የሚያጠቃልል ነው፡፡
21. **"የበዓል ቀናት"** ማለት አግባብ ባለው ህግ መደበኛ ስራ እንዳይሰራባቸው የተለዩ ሐይማኖታዊ እና ብሔራዊ በዓላት ናቸው፡፡
22. **"ደንብ"** ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 557/2016 ማለት ነው፡፡
23. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

### 1.3 የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ የአሰራር ማንዋል በየደረጃው በሚገኙ የመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበርና ቁጥጥር የስራ መደብ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

### 1.4 የባለስልጣኑ ራዕይ

በአዲስ አበባ ከተማ በ2022 ዓ.ም በመንገድ ተጠቃሚው ዘንድ ተቀባይነት ያለውና ሰላማዊ የትራፊክ እንቅስቃሴ ተረጋግጦ ማየት፣

### 1.5 የባለስልጣኑ ተልዕኮ

የመንገድ ደህንነት ግንዛቤን በማሻሻልና በማሳወቅ ደህንነቱ የተጠበቀ የመንገድ ተጠቃሚን መፍጠር፤ የመንገድ አጠቃቀምን በመወሰንና በመተግበር ፣ የትራንስፖርት ሥርዓትና የትራፊክ ቁጥጥርን በዘመናዊ

ቴክኖሎጂ በመምራት ፤ የትራፊክ ደንብና ስርዓት በማስከበርና የኩነት አስተዳደር ስርዓትን በማጎልበት የትራፊክ ፍሰት እና ደህንነት እንዲሻል ማድረግ ነው፡፡

## 1.6 የባለስልጣኑ እሴቶች

- ልኬት ላይ መመስረት፣
- ተጠቃሚውን ያገናዘበ ስራ
- ግልፀኝነትና
- ታማኝነት
- ተጠያቂነት
- ቅንጅታዊ አሰራር

## 1.7 ዓላማ

የዚህ የአሰራር ማንዋል መሠረታዊ አላማ የአዲስ አበባ ከተማ የትራፊክ ቁጥጥር የአፈጻጸም ወጥነትነት ያለው በማድረግ ግልፅ፣ ቀልጣፋ፤ ፍትሃዊ፤ ተደራሽ እና ተጠያቂነት ያለው የትራፊክ ቁጥጥር አገልግሎት መስጠት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡

### 1.6.1 ዝርዝር ዓላማዎች

1) የዲጅታል የትራፊክ ቅጣት አፈፃፀም ስርዓት ወጥነት ባለው አግባብ እንዲተገበር ማስቻል፣
2) በዲጅታል የትራፊክ ቅጣት አፈፃፀም ወቅት የሚፈጠሩ ችግሮችን መፍታት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፣
3) ከማዕከል እስከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ ያለውን የትራፊክ ቁጥጥር ተግባር ትስስር እንዲኖረው በማድረግ የትራፊክ ቁጥጥር ስራው ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ ለመምራት፤
4) በትራፊክ ቁጥጥር ተግባር ሲስተዋሉ የነበሩ የቁጥጥር ችግሮችን ለመፍታት፣ በባለቤትነት ለመከታተል፣ ለመደገፍና ለመቆጣጠር፤
5) በቁጥጥር ስራው ላይ ዋናኛ ተዋናይ የሆነውን የቁጥጥር ሰራተኞች ያላቸውን አቅምና ብቃት በመጠቀም ስራቸውን በሃላፊነትና በብቃትና በእውቀት እንዲወጡ ለማስቻል፤
6) የትራፊክ ቁጥጥር የስራ ክፍል የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በተሟላ መልኩ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለማስቻል፤
7) በትራፊክ ቁጥጥር ስራ ላይ ውጤታማ ያልሆኑ የሰው ኃይል ስምሪትና የግብዓት አጠቃቀም ብክነት ማስቀረት፣
8) በትራፊክ ቁጥጥር አሰራር ላይ የሚስተዋለውን የመልካም አስተዳደር ችግርና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል፣



Addis Ababa Traffic Management Authority

1.8 ግብ

በከተማው የትራፊክ ቁጥጥር ስራ ውስጥ የትራፊክ ቁጥጥር ተግባሩን ተገቢ በሆነ ሁኔታ መምራት፣ መቆጣጠር፣ መከታተልና መደገፍ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት እንዲፈጠር ማድረግ፡፡

## ክፍል ሁለት

## 2. የባለስልጣኑ መዋቅራዊ አደረጃጀትና የቁጥጥር ክፍሉ ተግባራት

### 2.1 የባለስልጣኑ መዋቅራዊ አደረጃጀት


የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን ከዚህ በፊት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 43/2007 መሠረት የተቋቋመ መንግስታዊ ተቋም ሲሆን በተለያዩ ጊዜያት የከተማ አስተዳደሩ አስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት ሲለዋወጥ አብሮ የመጣና በመጨረሻም የከተማ አስተዳደሩን አስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 መሠረት ወቅቱን ያማከለ ስልጣንና ተግባራት ተሰጠውት በዋና መስሪያቤት እና በ12 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተደራጀ መንግስታዊ ተቋም ሲሆን የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት አሉት፡፡

### 2.2 የባለስልጣኑ ስልጣንና ተግባራት

1. የትራፊክ አመራርና አስተዳደር ሥራ በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤ ለአገልግሎቱ ሥልጠት የሚያግዝ ስልት ይቀይሳል፤ ይተገብራል፤
2. የመንገድ ትራፊክን ማሳለጥ የሚያስችሉ ተግባራትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤
3. የመንገድ ትራፊክ ፍሰቱን በማሳለጥ ደህንነቱ የተጠበቀ የትራፊክ እንቅስቃሴ እንዲኖር የሚያስችል የትራፊክ ሥርዓት ይዘረጋል፤ ስታንዳርዶችን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
4. የትራፊክ ፍሰትና ደህንነትን ለማሻሻልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ሥርዓት ይዘረጋል፤ የመረጃ ሥርዓቱን በመጠቀም የትራፊክ ደህንነቱንና ፍሰቱን ይከታተላል፤ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ያቀናጃል፤ እንደአስፈላጊነቱ በግብዓትነት ይጠቀማል፤
5. በትራንስፖርት አገልግሎት እና በትራፊክ ሥርዓት ዙሪያ ግንዛቤ ይፈጥራል፤
6. የትራፊክ ምልክቶችና ማመላከቻዎች፣ የመንገድ ላይ ቀቦች፣ የትራፊክ መብራቶች እና ሌሎች የትራፊክ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን ይተገብራል፤ ያስተዳድራል፤
7. ከመንገድ ትራፊክ እንቅስቃሴ አንፃር ሊገነቡ የሚገባቸውን መንገዶች ይለያል፤ የመንገዶች ባለስልጣን የመንገድ ዲዛይን ሲሰራ ወይም ሲያሰራ ትራፊኩን ከማሳለጥ አኳያ አግባብነቱን ይገመግማል፤ ያረጋግጣል፤
8. የከተማዋን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ የጭነት ተሽከርካሪዎች መንቀሳቀሻ ፈቃድ ቁጥጥር ፤ የሞተር ብስክሌትና ሞተር አልባ ተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ መሆኑንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
9. መንገድ ለመዝጋትና ሌሎች ተዛማች ተግባራትን ወይም ከታለመለት ዓላማ ውጪ ለመጠቀም ለሚቀርብ ጥያቄ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ የመንገድ ላይ ኩነቶችን ያስተዳድራል፤ ህግን በሚተላለፉ ላይ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤


10. የትራፊክ ደንቦች መከበራቸውን ቁጥጥር ያደርጋል፤ አግባብ ባለው ህግ ደንብ ተላላፊዎችን ላይ እርምጃ ይወስዳል፤ የማስፈፀሚያ ስልቶችን ይዘረጋል፤ ተግባራዊነታቸውን ያረጋግጣል፤
11. የትራፊክ ፍሰትና ደህንነት ችግር ያለባቸውን መንገዶች ፣ መጋጠሚያዎችና አደባባዮችን በመለየት የማሻሻያ ስራ እንዲሰራ ያደርጋል፣
12. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልገሎት ክፍያ ያጠናል፤ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤
13. የአሽከርካሪዎችን የርቀት እይታ የሚጋርድ ወይም የደረቁ የመንገድ ዳርና የአደባባይ ዕጽዋት እንደአስፈሊጊነቱ በተፋሰስና አረንጓዴ አካባቢዎች ልማት ኤጀንሲ መወገዳቸውን ወይም መመልመላቸውን ያረጋግጣል፤
14. የሕዝብ የብዙኃን ትራንስፖርት፣ አንቡላንስና የእሳት አደጋ አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎችና የመሳሰሉት የመንገድ ቅድሚያና ያልተቋረጠ የትራፊክ አቅጣጫ የሚያገኙበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ መሆኑንም ይከታተላል፤
15. የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ ፍላጎትና አቅርቦት ጥናት አጥንቶ አማራጭ የመፍትሔ ሃሳቦችን ያቀርባል፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር ይተገበራል፤በመንግስት የለሙ የተሽከርካሪ ማቆሚያዎችን ያስተዳድራል፣በግልም ሆነ በመንግስት የለሙ የፓርኪንግ ቦታዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤ ህግን በሚተላለፉት ላይ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፣
16. በትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች ላይ የሚጣል ቅጣት አግባብ ባለው ህግ ይሰበስባል፤
17. የፓርኪንግ ቦታ ግንባታ ወይም አገልግሎት መስጠት ለሚፈልጉ የመንግስትና የግል ተቋማትና ግለሰቦች ፍቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፡፡
18. የትራፊክ መቆጣጠሪያ ማዕከል ያደራጃል ያስተዳድራል፣

## የዋና መ/ቤት መዋቅራዊ አደረጃጀት ስዕላዊ መግለጫ




## የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

## መዋቅራዊ አደረጃጀት ስዕላዊ መግለጫ




Addis Ababa Traffic Management Authority

### የቅርንጫፍ ጽ/ቤት የትራፊክ ቁጥጥር ቡድን የስራ ፍሰት




### 2.3 የትራፊክ ቁጥጥር፣ ኩነት አስተዳደር እና መድን ፈንድ ዳይሬክቶሬት ተግባር እና ኃላፊነት

- የዳይሬክተሩን ዝርዝር ዕቅዶች ያዘጋጃል፤
- የዳይሬክተሩን አፈጻጸም ይገመግማል፤
- ስራዎች በወጣላቸዉ ዕቅድ መሰረት መከናወናቸዉን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤
- በአሰራር የሚታዩ ክፍተቶችን በመለየት ክፍተቱን ለመሙላት የሚያስችሉ የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ይሰራል፤
- በትራፊክ ህግ ማስከበር ዙሪያ ያተኮረ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ለሚዘጋጅ ወርክሾፕ ዕቅድ ያቅዳል፤መድረክ ያመቻቻል፤የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ይሰራል፤ አፈጻጸሙን ይገመግማል፣
- የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለዳይሬክተር ያቀርባል፤

### 2.4 የትራፊክ ቁጥጥር ቡድን መሪ ተግባራት

- የኬዝ ቲሙን ሥራዎች በበላይነት ያቅዳል፣ ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ የሥራ አፈጻጸሙንም ይገመግማል፤
- በስሩ ያሉትን ፈፃሚዎች በጥራት፣ በቅልጥፍና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ተግባርና ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን ያረጋግጣል፤
- በኤጀንሲው የሚወጡ የመንገድ ትራፊክ ደኅንነት ደንብና መመሪያዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤
- በመንገድ ትራፊክ ደኅንነት ደንብና መመሪያ የትግበራ ሂደት የግብረ መልስ መረጃዎችን እንዲሰበሰቡና ለኤጀንሲው እንዲተላለፉ ያደርጋጋል፤

- የመንገድ ትራፊክ ሕግን በሚተላለፉት ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መወሰዱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
- የመንገድ ትራፊክ ፍሰቱን የሚያውኩ ቁሶች፣ ተረፈ ምርቶች፣ ማስታወቂያዎች እና ዕይታን የሚከለክሉ ሌሎች ነገሮች እንዲወገዱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤
- ህገ ወጥ የመንገድ ላይ ፓርኪንግን በወጣው ደንብና መመሪያ መሠረት ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፤
- የመንገድ ትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች መረጃ እንዲደራጁና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲሰራጩ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
- በትራፊክ መንገድ ላይ የእንስሳትና ሌሎች ሕገ-ወጥ የንግድና የምርት ዝውውሮች እንዳይፈጸሙ የሚከለክሉ ደንብና መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ የክትትልና የቁጥጥር ተግባራት እንዲከናወኑ ያደርጋል፤
- በትራፊክ የመረጃ ማዕከልና በራዳር እንዲሁም በተዘዋዋሪ ተሽከርካሪዎች (patrol) በመታገዝ የዕለት ተዕለት የትራፊክ ፍሰቱ ላይ ክትትልና ቁጥጥር እንዲካሄድ ያደርጋል፤
- በትራፊክ መንገዶች ላይ እና ተያያዥ በሆኑ ቦታዎች የሚደረጉ የተለያዩ ክዋኔዎች በመመሪያው መሠረት ፍቃድ ያገኙ መሆናቸውንና በተሰጣቸው ፈቃድ መሠረት መጠቀማቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
- የትራፊክ አደጋና ሌሎች በመንገድ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች ሲከሰቱ ተጎጂዎች የድንገተኛ አደጋ አገልግሎት (Emergency Service) እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ይሰራል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
- የሚቀርቡ ቅሬታዎች በተዘረጋው የቅሬታ አፈታት ሥርዓት መሰረት መስተናገዳቸውን ያረጋግጣል፤
- የኬዝቲሙን የሥራ አፈጻጸም በተመለከተ ለቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፤
- ከቅርብ ኃላፊው የሚሰጡትን ሌሎች ተጨማሪ ሥራዎች ያከናውናል፤

## 2.5 የመንገድ ትራፊክ ቁጥጥር ቡድን አስተባባሪ

- የመንገድ ትራፊክ ፍሰት እና የደህንነት ችግር የሚያስከትሉ ደንብ ጥሰቶችን መቆጣጠር፣
- ምድብ የተሰጣቸውን የትራፊክ ቁጥጥር ሠራተኞች ተግባራቸውን በአግባቡ መከወናቸውን መከታተል መቆጣጠር
- ከትራፊክ ቁጥጥር ሰራተኞች የውሎ እና የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት መቀበል ግብረ መልስ መስጠት
- ለትራፊክ ቁጥጥር ቡድን ወቅታዊ ሪፖርት በማዘጋጀት ማቅረብ
- የትራፊክ ቁጥጥር ሠራተኞች ከደንብ ተላላፊዎች የተረከቡዋቸውን አሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እና ሰሌዳ በመሰብሰብ ገቢ ማድረግ
- ከደንብ ተላላፊዎች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በመቀበል በራሱ መፈታት የሚችሉትን መፍታት



Addis Ababa Traffic Management Authority

- ሌሎች በቅርብ ኃላፊ ተለይተው የሚሰጡ ህጋዊ ተግባራትን ማከናወን
- የመንገድ ትራፊክ ፍሰት እና የደህንነት ችግር የሚያስከትሉ ደንብ ጥሰቶች ቁጥጥር ስራ ያስተባብራል፣
- የትራፊክ ቁጥጥር ስራ ዕቅድና የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት የጋራ ያደርጋል፤
- የቁጥጥር ስራ ማስፈፀሚያ መርጃ መሳሪያዎች መሟላታቸዉንና ዝግጁ መሆናቸዉን ያረጋግጣል፡፡
- የትራፊክ ቁጥጥርየሚካሄድባቸውን መንገዶች (ቦታዎች) ለተቆጣጣሪዎች ያከፋፍላል፤ የስራ ስምሪት ይሰጣል፡፡
- ተቆጣጣሪዎች በተመደቡበት የስምሪት ቦታ የዕለተዕለት ስራዎቻቸዉን ይከታተላል፤
- የትራፊክ ፍሰት የሚጨናነቅባቸውን መንገዶች፣ አደባባዮች፣ መጋጠሚያ ቦታዎች ላይ ያለዉን የትራፊክ እንቅስቃሴ ቁጥጥር ስራ ያስተባብራል፡፡
- መንገድ ላይ የፓርኪንግ ችግር የሚያስከትሉ እንዲሁም ለትራፊክ አደጋ የሚያጋልጡ ደንብ ጥሰቶች ቁጥጥርን ክትትል ያደርጋል፣
- በትራፊክ ቁጥጥር ስራ መስክ ላይ የሚያጋጥሙ ከተቆጣጣሪ አቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮችን በመለየት ከሚከለከተዉ ጋር በጋራ በመሆን መፍትሄ እንዲያገኝ ያደርጋል፤
- አጠቃላይ የትራፊክ ቁጥጥር ስራዎች የክትትል፤ድጋፍ እና ግምገማ በማድረግ ሪፖርት ያዘጋጃል፣
- ከቅርብ ሀላፊዉ የሚሰጡ የስራ መመሪያዎችን ይተገብራል፡፡

## 2.6 የትራፊክ ቁጥጥር ሽፍት ሱፐርቫይዘር

- የመንገድ ትራፊክ ፍሰት እና የደህንነት ችግር የሚያስከትሉ ደንብ ጥሰቶችን መቆጣጠር፣
- ዕቅድና የድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀትና የጋራ ማድረግ
- ቁጥጥር የሚካሄድባቸውን መንገዶች (ቦታዎች) ለተቆጣጣሪዎች ማከፋፈል
- በቁጥጥር ስራ ማስፈፀሚ መርጃ መሳሪያዎችን ማሟላትና ዝግጁ ማድረግ

## 2.7 ከፍተኛ የትራፊክ ተቆጣጠሪ

- በሥራ መደቡ የሚከናወኑ ተግባራት፡-
- የመንገድ ትራፊክ ፍሰት የሚጨናነቅባቸውን መንገዶች ላይ የትራፊክ ቁጥጥር ስራ ይሰራል፡፡
- አደባባዮች፣ መጋጠሚያ ቦታዎችንና መንገድ ላይ የፓርኪንግ ችግር የሚያስከትሉ እንዲሁም ለትራፊክ አደጋ የሚያጋልጡ ደንብ ጥሰቶችን ይቆጣጠራል፣
- የተሽከርካሪ ማቆሚያ ፓርኪንግ ቦታዎችን ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
- የትራፊክ ደንብ ተላላፊ አሽከርካሪዎችን ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል፡፡
- የትራፊክ ደንብ ተላልፈዉ የተገኙ አሽከርካሪዎች ላይ የጥፋት ሪከርድ በመጻፍ የቅጣት ቻርጅ ይሰጣል፡፡

- የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በመቀበል ያረጋግጣል፡፡
- የትራፊክ ደንብ ተላላፊ አሽከርካሪው በቦታው ካልተገኘ እርምጃ እንዲወሰድበት የተሽከርካሪዉን ስሌዳ በመፍታት ያስተላልፋል፤
- ከቅርብ ሀላፊዉ የሚሰጡ የስራ መመሪያዎችን ይተገብራል፡፡
- መካከለኛ የትራፊክ ተቆጣጠሪ
- በሥራ መደቡ የሚከናወኑ ተግባራት፡-
- የመንገድ ትራፊክ ፍሰት የሚጨናነቅባቸውን መንገዶች ላይ የትራፊክ ቁጥጥር ስራ ይሰራል፡፡
- አደባባዮች፣ መጋጠሚያ ቦታዎችንና መንገድ ላይ የፓርኪንግ ችግር የሚያስከትሉ እንዲሁም ለትራፊክ አደጋ የሚያጋልጡ ደንብ ጥሰቶችን ይቆጣጠራል፣
- የተሽከርካሪ ማቆሚያ ፓርኪንግ ቦታዎችን ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
- የትራፊክ ደንብ ተላላፊ አሽከርካሪዎችን ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል፡፡
- የትራፊክ ደንብ ተላልፈዉ የተገኙ አሽከርካሪዎች ላይ የጥፋት ሪከርድ በመጻፍ የቅጣት ቻርጅ ይሰጣል፡፡
- የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በመቀበል ያረጋግጣል፡፡
- የትራፊክ ደንብ ተላላፊ አሽከርካሪው በቦታው ካልተገኘ እርምጃ እንዲወሰድበት የተሽከርካሪዉን ስሌዳ በመፍታት ያስተላልፋል፤
- ከቅርብ ሀላፊዉ የሚሰጡ የስራ መመሪያዎችን ይተገብራል፡፡
- 2.8 ጀማሪ የትራፊክ ተቆጣጣሪ
- በሥራ መደቡ የሚከናወኑ ተግባራት፡-
- የመንገድ ትራፊክ ፍሰት የሚጨናነቅባቸውን መንገዶች ላይ የትራፊክ ቁጥጥር ስራ ይሰራል፡፡
- አደባባዮች፣ መጋጠሚያ ቦታዎችንና መንገድ ላይ የፓርኪንግ ችግር የሚያስከትሉ እንዲሁም ለትራፊክ አደጋ የሚያጋልጡ ደንብ ጥሰቶችን ይቆጣጠራል፣
- የተሽከርካሪ ማቆሚያ ፓርኪንግ ቦታዎችን ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
- የትራፊክ ደንብ ተላላፊ አሽከርካሪዎችን ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል፡፡
- የትራፊክ ደንብ ተላልፈዉ የተገኙ አሽከርካሪዎች ላይ የጥፋት ሪከርድ በመጻፍ የቅጣት ቻርጅ ይሰጣል፡፡
- የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በመቀበል ያረጋግጣል፡፡
- የትራፊክ ደንብ ተላላፊ አሽከርካሪው በቦታው ካልተገኘ እርምጃ እንዲወሰድበት የተሽከርካሪዉን ስሌዳ በመፍታት ያስተላልፋል፤
- ከቅርብ ሀላፊዉ የሚሰጡ የስራ መመሪያዎችን ይተገብራል፡፡



የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን
Addis Ababa Traffic Management Authority

## 2.8 ሲስተም ባለሙያ

በሥራ መደቡ የሚከናወኑ ተግባራት፡-

- ከባድ የአካል ጉዳት ያደረሱ አሽከርካሪዎች መረጃ ተቀብሎ ይመዘግባል፤የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይረከባል፡፡
- ተደጋጋሚ የትራፊክ ደንብ በመተላለፍ ነጥብ የተመዘገበባቸዉ (Point Penality) እና የትራፊክ ደንብ በመተላለፍ ከባድ የአካል ጉዳት ያደረሱ አሽከርካሪዎች እገዳ አገልግሎት ይሰጣል፤
- የእግድ አገልግሎት ጥያቄ ተቀብሎ የደንብ ተላላፊ መረጃ ያጣራል፡፡
- የትራፊክ ደንብ በመተላለፍ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የታገደባቸዉ አሽከርካሪዎች የእግድ ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡
- የትራፊክ ደንብ በመተላለፍ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የታገደባቸዉ አሽከርካሪዎች መረጃ ማደራጀትና ሪፖርት ማዘጋጀት፡፡
- ከአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ጋር በተያያዘ የእግድ ይጣራልኝ ጥያቄ መቀበል፤ ማጣራት፤ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸዉን በማረጋገጥ ከእግድ ነጻ ማስረጃ ይሰጣል፡፡
- የእግድ ጊዜያቸዉን ያጠናቀቁ አሽከርካሪዎች የእግድ ይነሳልኝ ጥያቄ ተቀብሎ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸዉን በማረጋገጥ እግድ የማንሳት አገልግሎት ይሰጣል፡፡
- የሞተር ብስክሌት እንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ ሲስተም አገልግሎት ይሰጣል፡፡
- የሞተርሳይክል ጂፒኤስ እና ፍጥነት መገደቢያ ገጣሚ ድርጅቶችን ገጠማ ሲስተም ላይ ያረጋግጣል፡፡
- የሞተርሳይክል መንቀሳቀሻ ፈቃድና እድሳት አገልግሎት ይሰጣል፡፡
- ጂፒኤስ የገጠሙ ሞተርሳይክሎችን በመቆጣጠሪያ ሲስተም ላይ ክትትል ያደርጋል፡፡
- ከመቆጣጠሪያ ሲስተም ዉጪ የሆኑ ሞተርብስክሌቶችን በመለየት እና መረጃዎቻቸዉን በማደራጀት እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ ለሚመለከተዉ ክፍል ሪፖርት ያደርጋል፡፡

## 2.9 የማዕከል ትራፊክ ቁጥጥር ቡድን ተግባራት

- የማእከል የመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበርና ቁጥጥር ባለሙያ በቢፒአር ጥናት የተቀመጡ ተግባርና ሃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትን ተግባራ ያከናውናል፡-
- በዋና ዋና መስመሮች ላይ በጠዋትና ማታ መርሀ ግብር የትራፊክ ቁጥጥርና ፍሰት የማሳለጥ ተግባራትን ያከናውናል
- በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ስራዎች ያከናውናል
- በመስክ ድጋፍና ክትትል ስራዎች ያገኛቸውን ግኝቶች ግብረ መልስ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይሰጣል
- ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ጋር በመቀናጀት በጥናት ላይ የተመሰረተ የቁጥጥር ስራ ይሰራል


## 2.10 የትራፊክ ቁጥጥር ባለድርሻ አካላት እና ፍላጎታቸው

- የመንገድ ተጠቃሚዎች እና ባለድርሻ አካላቱ የሚጠብቁት ዋንኛ ተግባራት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ህጎችን በሚተላለፉ አሽከርካሪዎች ላይ ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ እንዲሁም ከባለድርሻ አካላቱ ለሚቀርቡ ጥቄዎች ምላሽ በመስጠት  ለመንገድ ተጠቃሚው ግልፅና ተጠያቂነት ያለው የትራፊክ ቁጥጥር ስራ በማከናወን  ፍላጎታቸውን ማርካት ነው፡፡
- በመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበርና ቁጥጥር ተግባር ላይ በባለድርሻ አካልነት የተለዩት የመንገድ ተተቃሚዎች፣ የአዲስ አበባ ከተማ የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድ ቁጥጥር ባለሥልጣን፣ የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን፣ የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን፣ የፌደራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን፣ የአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ፅ/ቤትና ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የመሣሠሉትን ባለድርሻ አካላት የያዘ ነው፡፡
- የመንገድ ተተቃሚዎች ደህንነታቸው ተጠበቀና ፍሰቱ ተሳለጠ የትራፊክ እንቅስቃሴ እንዲኖር የትራፊክ ቁጥጥር ሥራው ወሳኝ ጉዳይ  ሲሆን በቁጥጥሩ ወቅት የትራንስፖርት ደንብን በሚጥሱና በሚተላለፉ አሽከርካሪዎች፤ ላይ ተከታታይነት እና ወጥነት ያለው የትራፊክ ቁጥጥር የአሠራር ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ ተገቢነት ያለው ሲሆን የትራንስፖርት ህግን በሚጥሱና በሚተላለፉት ላይ ተገቢ እርምጃዎችን በመውሰድ በከተማው ውስጥ የሚኖረውን የትራፊክ እንቅስቃሴ ደህንነቱ የተጠበቃ ከማድረግ ባለፈ የትራፊክ ቁጥጥር ስራው ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡
- በመሆኑም የከተማውን  የመንገድ ተጠቃሚና የባለድርሻ አካላቱን ፍላጎትና ጥቄዎች በተገቢው ሁኔታ ለመመለስና ለማርካት ይረዳ ዘንድ በትራፊክ ቁጥጥር ተግባሩ ላይ የባለድርሻ አካላቱን መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለይቶ ማስቀመጥ ተገቢነት ያለው ሲሆን  ዋና ዋናዎቹም ፡-
- ደህንነቱ የተጠበቀ የትራንስፖርት እንቅስቃሴ እንዲፈጠር ማድረግ
- የመንገድ ተጠቃሚውን ፍላጎት ማዕከል ያደረገ አገልግሎት መስጠት
- የትራንስፖርት ህግንና ደንብን በማያከብሩ አሽከርካሪዎች ላይ ወጥ የሆነ እርምጃ መውሰድ
- በተግባር የሚገለፅ ሙያዊ ሥነ-ምግባር የተላበሰ የትራፊክ ቁጥጥር ስራ ማከናወን

Addis Ababa Traffic Management Authority

## የመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበርና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ውጫዊ ትስስር

2.11



## 2.11.1 2.8 የትራፊክ ቁጥጥር ቡድን ባለድርሻ አካላት እና የሥራ ሂደቱ ሚና

| ተ.ቁ | የኤጀንሲው ባለድርሻ አካላት | የባለ ድርሻ አካላት ሚና | የኤጀንሲዉ ሚና | ከትስስሩ የሚጠበቁው ጤቶች |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን | • የባለሙያ እና የህግ ጥፋት የፈፀሙ ተሽከርካሪዎች መረጃ ድጋፍ<br>• ህግ ማስከበር ስራ መስራት<br>• አደጋን መቀነስ<br>• ፍሰትን ማሻሻል<br>• መቆጣጠሪያ ማዕከሉ በሚያስተዳድራቸው መንገዶች ላይ ወንጀሎች ሲፈፀሙ የማሳወቅ እና የተንቀሳቃሽ<br>• ምስሎች ማረጋገጫ መስጠት | • የረዳት የትራፊክ አሰልጣኝ መጠይቅ፣ የትራፊክ አደጋ መረጃ ማግኘት<br>• የህግ ጥሰት የፈጸሙትን ተሽከርካሪዎች መለያ መቀበል<br>• የተሰሩ የተሽከርካሪ ማቆሚያዎች በጋራ ማስተዳደር<br>• የሚተገበሩ የኦፕሬሽን ስራዎች ማሳወቅና በጋራ መስራት | • ጥራቱን የጠበቀ ስልጠና እና ጥራቱን የጠበቀ መረጃ ማግኘት<br>• የህግ ጥሰት የፈጸሙ መኪኖች ላይ የተወሰዱ የህግ እርማጃዎች<br>• ደህንነቱ የተረጋገጠና ጤናማ የትራፊክ ፍሰት |
| 2 | የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን | • በእግረኞች መንገድ አጠቃቀም ችግር የሚፈጥር ግንባታ ላይ<br>• አዲስ በሚገነባቸው መንገዶች ላይ የትራፊክ መቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂዎችን መትከል<br>• ቀድሞ የተተከሉ ቴክኖሎጂዎች በጥገና ወቅት ጥበቃ እንዲከናወንላቸው ማስደረግ | • በእግረኞች መንገድ አጠቃቀም ችግር የሚፈጥር ግንባታ ላይ በጋራ መስራት<br>• መንገዶች ከመገንባታቸው እና ከመጠገናቸው በፊት የማሳወቅ ስራ<br>• የመንገድ ዳር ተሽከርካሪ ማቆሚያ በጋራ የመስራት ፍላጎት<br>• በጋራ የመስራት ፍላጎት<br>• የመንገድ ትራፊክ ፍሰት ማሻሻያ ስራዎችን በጋራ መስራት፡፡ | • የእግረኛ መንገድ አጠቃቀም ላይ ግንባታ በጋራ መፍታት<br>• ዘመናዊ የትራፊክ ቴክኖሎጂዎች የተተከለላቸው መንገዶች<br>• በሚጠበቀዉ መንገድ የሚሰሩ የትራፊክመቆጣጠሪያቴክኖሎጂዎች<br>• ደህንነቱ የተረጋገጠና ጤናማ የትራፊክ ፍሰት<br>• የተሰራና የተጠገነ መንገድ |
| 3 | የፌደራል ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር | • የባለሙያ ፣ መረጃ እና ሌሎች የፖሊሲ አቅጣጫን የተከተሉ ስትራቴጂክ እቅድ፣ የመመሪያ ወዘተ.. ድጋፍ ማድረግ | • ውሳኑ የሚሹ ጉዳዮች ማቅረብና ማስወሰን<br>• የሚተገበሩ የኦፕሬሽን ስራዎች ማሳወቅና በጋራ መስራት፣ | • በመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ያለው ህብረተሰብ መፍጠር<br>• የተሳለጠና ደህንነቱ የተጠበቀ የመንገድ ትራፊክ ፍሰት |
| 4 | የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን | • የመንገድ ደህንነት ትምህርት በተሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት መካተት<br>• የተሽከርካሪ ፍተሻና ጥራት ማስጠበቅ<br>• የመንጃ ፈቃድ አሰጣጥ ቁጥጥር ሲስተም መዘርጋት (avoid forgery) | • የመንገድ ድህንነት ትምህርት በተሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ተካትቶ መሰጡትን ማረጋገጥ<br>• በደንብ መተላለፍ ጥፋት ሚፈለጉ ተሽከርካሪዎችን ማሳወቅ | • የመንገድ ድህንነት ትምህርት በተሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ተካትቱ መሰጠቱን<br>• በደንብ መተላለፍ ጥፋት የሚፈለጉ ተሽከርካሪዎች ተለይተው መቅረባቸው፣ |

| ተ.ቁ | የኤጀንሲው ባለድርሻ አካላት | የባለ ድርሻ አካላት ሚና | የኤጀንሲዉ ሚና | ከትስስሩ የሚጠበቁው ጤቶች |
|---|---|---|---|---|
| | | • በደንብ መተላለፍ ጥፋት የሚፈለጉ ተሽከርካሪዎችን ባለንብረት በመለየት ለኤጀንሲው ማሳወቅ<br>• በደንብ መተላለፍ ጥፋት የሚፈለጉ ተሽከርካሪዎች ቦሎ እንዳያድሱ መከላከ | | |
| 5 | የአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ፅ/ቤት | • ህግ ማስከበር<br>• የህግ ጥሰት የፈፀሙ ግለሰቦችን ምኞ መስጠት | • የሚተገበሩ የኦፕሬሽን ስራዎች ማሳወቅና በጋራ መስራት<br>• የህግ ጥሰት ፈፀሙ ድርጅቶችና ግለሰቦችን መረጃ መቀበል | • የህግ ጥሰት የፈጸሙ ግለሰብና ድርጅቶች ላይ የተወሰዱ የህግ እርማጃዎች<br>• ደህንነቱ የተረጋገጠና ጤናማ የትራፊክ ፍሰት |
| 6 | የአ/አ/ከ/ አስ/ አቃቢ ህግ ቢሮ | • የህግ ማርቀቅና ስርፀት ትግባራት ማከናወን<br>• ህግ ማስከበር | • የሚዘጋጁ የህግ ሰነዶችን ማሳወቅ<br>• የህግ ረቂቅ ዝግጅት ላይ በጋራ መስራት | • ጥራቱን የጠበቀ የህግ ሰነድ ዝግጅት<br>• ጥራቱን የጠበቀ የስርፀት ስራ መስራት |
| 7 | አአ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ | • ቢሮው በትስስሩ ሂደት በቋሚነት በመገናኘት በስሩ የሚገኙ ተቋማትን አፈፃፀም በጋራ ተገኝቶ መገምገም ችግሮችን በመለየት አቅጣጫ እያስቀመጡ መሄድ<br>• በቢሮ ደረጃ ቀርበው ውይይት ሊደረግባቸውና ውሳኔ የሚያሻቸውን ጉዳዮች ውሳኔ እንደሰጥባቸው ማድረግ<br>• ህግ በመተላለፍ የሚያመልጡ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሚሰጉ ተሽከርካሪዎች በመያዝ ለኤጀንሲው ማስተላለፍ | • በትስስሩ ሂደት አፈፃፀም በጋራ ተገኝቶ መገምገም ችግሮችን በመለየትየሚቀመጡ መፈፀም<br>• በቢሮ ደረጃ በተያት የሚገባቸው ጉዳዮች ለይቶ ማቅረብ፣ ማስወሰን እና መፈፀም<br>• ህግ በመተላለፍ የሚያመልጡ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች መረጃ ለቢሮው ማቅረብ | • የተሳለጠና ደህንነቱ የተጠበቀ የመንገድ ትራፊክ ፍሰትን ማረጋገጥ |

## ክፍል ሶስት

## 3. የትራፊክ ቁጥጥር ስራ አጠቃላይ መርሆዎች

የከተማው የትራፊክ ቁጥጥር ስራ ወጥነት ባለው መልኩ በስርዓት እንዲመራ መደረጉ የሚሰጠውን አገልግሎት ውጤታማ ከማድረግ አኳያ የራሱ ጉልህ ሚና ይጫወታል፡፡ ስለሆነም የትራፊክ ቁጥጥር ስራው ወጥነትነት ያለው በማድረግ ግልፅ፣ ቀልጣፋ፤ ፍትሃዊ፤ ተደራሽ እና ተጠያቂነት ያለበት እንዲሆን ከዚህ በታች በተዘረዘሩ መርሆዎች መሠረት መፈፀም ይኖርበታል፡፡

### 3.1 ህግና ስርዓትን የመከተል መርህ

የትራፊክ ቁጥጥር ስራ ህግ የማስከበር ተግባር እንደመሆኑ መጠን መፈፀም ያለበት ህግና ስርዓትን በተከተለ አግባብ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህም የትራፊክ ተቆጣጣሪው ደንብ ተላላፊውን በህጉ እና በህጉ በተቀመጠው መሠረት ብቻ ከማስተናገድ ያለፈ ሚና አይኖረውም፡፡

በህጉ የተቀመጠውን ቅጣት በደንብ ተላላፊው ላይ ለመጣል ትራፊክ ተቆጣጣሪው ከአንድ የመንግስት ሠራተኛ ወይም አገልጋይ የሚጠበቀውን የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት መከተል ይኖርበታል፡፡

ለዚህም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ፣ በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪ ደንብ፣ በትራፊክ ቅጣት አፈፃፀም መመሪያ፣ በትራፊክ ቁጥጥር ሠራተኞች የስነ ምግባር መመሪያ እና ሌሎች ህጎች የተጣሉ ግዴታዎችን በማክበር መሆን አለበት፡፡

የትራፊክ ቅጣት የሚጣለው በጥፋት እና በጥፋት ላይ ብቻ በመመስረት ነው፡፡ ይህም የትራፊክ ተቆጣጣሪው ደንብ ተላላፊውን በህጉ በተቀመጠው መሠረት ከማስተናገድ በተጨማሪ የሚጣለው ቅጣት በማናቸውም ምክንያት ቢሆን በህጉ ከተቀመጠው መብለጥም ሆነ ማነስ አይኖርበትም፡፡

የትራፊክ ተቆጣጣሪው ተግባሩን በመልካም ስነ ምግባር ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡የትራፊክ ቁጥጥር ስራዎች ሁሉ ለህጉ እና ለህሊና በማይፃረር መልኩ መፈፀም ያለባቸው ሲሆን ትራፊክ ተቆጣጣሪው የተለየ ወረታን ወይም ጥቅምን በማሰብ፣ ጉቦ በመጠየቅ ወይም በመቀበል ደንብ ተላላፊውን ከቅጣት ነፃ ለማድረግ መሞከር ለተጠያቂነት የሚዳርገው መሆኑን ተረድቶ ራሱን ከመሰል ያልተገቡ ድርጊቶች መቆጠብ አለበት፡፡

### 3.2 ሰብአዊ ክብርን የመጠበቅና ከአድሎ የፀዳ መሆን

የትራፊክ ተቆጣጣሪው ህግ የማስከበር ስራ በሚያከናውንበት ወቅት በደንብ መተላለፍ ጥፋት የሚያገኛቸውን ደንብ ተላላፊዎች ተገቢውን አክብሮት በማሳየት፣ የፈፀሙትን ጥፋት በትክክል የመግለፅና የማሳወቅ ወይም የማስረዳት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ትራፊክ ተቆጣጣሪው ተግባሩን ሲያከናውን ለደንብ ተላላፊዎች እና ለመንገድ ተጠቃሚዎች ሙያው የሚጠይቀውን ተገቢውን አክብሮት የማሳየት ሃላፊነት የሚኖርበት ሲሆን በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ደንብ ተላላፊውን ማመናጨቅ ወይም መሳደብ የለበትም፡፡ የትራፊክ ተቆጣጣሪው የትራፊክ ቅጣት ወረቀት ጽፎ ለመስጠት በሚያደርገው ሂደት ደንብ ተላላፊው ለሚያሳየው ያልተገባ ባሕሪ ከመንግስት ሠራተኛ የሚጠበቀውን



Addis Ababa Traffic Management Authority

ባህሪ ከማሳየትና አስፈላጊ መረጃዎችን በጥንቃቄ ከመያዝና ለቅርብ ኃላፊ ከማሳወቅ ያለፈ በስሜታዊነት ማናቸውንም ያልተገባ ድርጊት መፈፀም የለበትም፡፡

የትራፊክ ተቆጣጣሪው የትራፊክ ቁጥጥር ስራ በሚያከናውንበት ወቅት በማንኛውም መመዘኛ ቢሆን በደንብ ተላላፊዎች መካከል ልዩነት መፍጠር የለበትም፡፡

የደንብ መተላለፍ ቅጣት በሚጣልበት ወቅት ተመሳሳይ ጥፋት ለፈፀሙ ደንብ ተላላፊዎች የተለያየ ቅጣት መጣል ወይም አንደኛውን በመቅጣት ሌላኛውን ሳይቀጡ ማለፍ የለበትም፡፡

## 3.3 በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነትን ማረጋገጥ

የትራፊክ ቁጥጥር ስራዎች የሚከናወኑት በመንገድ ላይ እንደመሆኑ መጠን ተግባሩ በመንገድ ላይ ለሚንቀሳቀስ ህብረተሰብ ክፍል ሁሉ ክፍት እና የሚታይ መሆኑ የታመነ ነው፡፡

በዚህ ሂደት ትራፊክ ተቆጣጣሪው የሚያከናውናቸው በጎም ሆኑ መጥፎ ተግባራት ለህብረተሰቡ በግልፅ የሚታዩ መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ ስለሆነም የትራፊክ ተቆጣጣሪው ተግባር/ድርጊት ሁልጊዜም ቢሆን በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው እና የሚደገፉ እንዲሆኑ ጥረት ከማድረግ ባለፈ በግልፅ የሚታይና ከአጉል ጥርጣሬ የጸዳ እንዲሆን ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

የትራፊክ ተቆጣጣሪ የትራፊክ ደንብ የተላለፈ አሽከርካሪ ባጋጠመው ጊዜ በንቃትና በጥንቃቄ አሽከርካሪውን ተገቢውን ምልክት/ስቶፐር በማሳየት እንዲቆም መጠየቅ አለበት፡፡ በተሰጠው ምልክት ወይም ትእዛዝ መሰረት የቆመን ተሽከርካሪ ተገቢውን ሰላምታ በመስጠት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን በመጠየቅ አሽከርካሪው ከተሽከርካሪው ሳይወርድና ሳይንገላታ በአጭር ደቂቃ ውስጥ የቅጣት ወረቀት ጽፎ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

## 3.4 ቴክኖሎጅ የተደገፈ አገልግሎት መስጠት

የትራፊክ ቅጣት አፈፃፀምና አሰባሰብ ከጊዜ ወደ ጊዜ በዘመናዊ ቴክኖሎጅ እየተደገፈና እየዘመነ በመሄድ ላይ ይገኛል፡፡ የትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች በዲጅታል የትራፊክ ቅጣት ማስፈፀሚያ ሲስተም መሠረት በኤሌክትሮኒክ መንገድ የሚላከላቸውን የቅጣት ትኬት መሠረት በማድረግ በቴሌ ብር ፣ ኢ ብር እና ሌሎች አማራጮች የመክፈል ሂደቶች ተግባራዊ እየተደረጉ በመሆኑ የትራፊክ ተቆጣጣሪው በተለያዩ ጊዜያት ተግባራዊ የሚደረጉ የትራፊክ ቅጣትን በቴክኖሎጅ የመክፈል አሰራሮች ጋር እራሱን እያላመደና እያበቃ መሄድ ይጠበቅበታል፡፡

# ክፍል አራት

## 4. የትራፊክ ቁጥጥር አሰራር፣ የግብዓት አጠቃቀም እና የዲሲሰፕሊን ሁኔታ

### 3.5 የትራፊክ ቁጥጥር የአሰራር ማንዋሉ ዝግጅትና ይዘት

በከተማው የትራፊክ ቁጥጥር ስራ ላይ የሚስተዋሉትን ክፍተቶች በመለየትና የሚሰጠውን አገልግሎት በተሟላና ስርዓት ባለው መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡ የዚህ አሰራር ማንዋል አጠቃላይ ይዘት በማዕከልና ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የትራፊክ ቁጥጥር ተግባር ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ባለሙያዎችና አመራሮችን በማቀናጀት ወጥነት ያለው የትራፊክ ቁጥጥር ስራ መስራት የሚቻልበትን ስርዓት ለመፍጠር ነው፡፡

በመሆኑም በዚህ የአሰራር ማንዋል መግቢያ ላይ በግልጽ የተቀመጡትን መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮች መነሻ በማድረግ በቀጣይ በትራፊክ ቁጥጥር ተግባራት ላይ የሚኖረውን ስራ ባለው የሰው ሃይል፣ ግብዐትና ሌሎች አቅሞችን አሟጦ በመጠቀም በተሟላ መልኩ ተግባሩን ለማስፈጸም የሚያስችል ነው፡፡

በዚሁ መሰረት ከዚህ ቀጥሎ በየደረጃው በማዕከል፣ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በተለይም በትራፊክ ተቆጣጣሪው ሊተገበሩና ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባራትን በግልጽ በመለየት፣ በማደራጀት በትራፊክ ቁጥጥር ስራ ላይ ሊኖራቸው የሚገባውን ተግባርና ሃላፊነታቸውን በቅንጅት መወጣት በሚችሉበት መልኩ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

### 3.6 የትራፊክ ቁጥጥር የስራ ክፍል አደረጃጀት

የመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበርና ቁጥጥር የስራ ክፍል ከማዕከል እስከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተደራጀ ነው፡፡ በማዕከል ደረጃ፣ 1 የመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበርና ቁጥጥር ዳይሬክተር፣ 1 የመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበርና ቁጥጥር ቡድን መሪ፣ 3 የመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበርና ቁጥጥር ከፍተኛ ባለሙያዎች፣ 3 የመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበርና ቁጥጥር ባለሙዎች III ፣ 3 የመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበርና ቁጥጥር ከፍተኛ ባለሙያዎች፣ 4 የመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበርና ቁጥጥር ባለሙዎች II ፣ 3 የመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበርና ቁጥጥር ከፍተኛ ባለሙያዎች፣ 3 የመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበርና ቁጥጥር ባለሙዎች I በድምሩ 16 ሠራተኞችን ያቀፈ ሲሆን በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደረጃ በእያንዳንዱ የቅርንጫፍ ጽ/ቤት 1 ስራ አስኪያጅ ፣1 ዳይሬክተር ፣ 2 የትራፊክ ቁጥጥር ቡድን መሪ እንዲሁም የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ እንደሚሸፍነው ክፍለ ከተማ ስፋት የሚለያይ የቡድን አስተባባሪዎች እና የትራፊክ ቁጥጥር ሠራተኞች ይገኛሉ፡፡ በዚህ መሰረት የቡድን አስተባባሪን በተመለከተ ለአራዳ ቅ/ጽ/ቤት 10 ትራፊክ ተቆጣጣሪ 104፣ ለልደታ ቅርንጫፍ 6 ቡድን አስተባባሪና 58 ተቆጣጣሪ፣ ለቂርቆስ ቅርንጫፍ 12 አስተባባሪና 116 ተቆጣጣሪ፣ 4 አስተባባሪና 64 ተቆጣጣሪ፣ ለጉለሌ ቅርንጫፍ 8 አስተባባሪና 70 ተቆጣጣሪ፣ ለየካ ቅርንጫፍ 8 አስተባባሪና 76 ተቆጣጣሪ፣ለቦሌ ቅርንጫፍ 28 አስተባባሪና 318 ተቆጣጣሪ፣ ለኮልፌቀራንዮ ቅርንጫፍ 16 አስተባባሪና 146 ተቆጣጣሪ፣ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅርንጫፍ 20 አስተባባሪና 201 ተቆጣጣሪ፣ለአቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ 16 አስተባባሪና 154 ተቆጣጣሪ እንዲሁም ለለሚኩራ ቅርንጫፍ 28 አስተባባሪና 312 ተቆጣጣሪ ተመድበዋል፡፡



Addis Ababa Traffic Management Authority

## 3.7 የትራፊክ ቁጥጥር መጀመሪያና መጨረሻ

የትራፊክ ቁጥጥር ስራ የሚጀምረው የትራፊክ ተቆጣጣሪ ሠራተኛው በተመደበበት ቦታ ከደረሰ ጀምሮ ሲሆን የሚያበቃውም የተመደበለትን የስራ ሰዓት አጠናቆ ከስምሪት ቦታው ሲለቅ ነው:: የትራፊክ ተቆጣጣሪው ለቁጥጥር ስራ የሚሰማራበት ቦታ እና ጊዜ በየጊዜው የሚቀያየር ሆኖ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የመንገድ ደህንነት ግንዛቤና ደንብ ማስከበር ዳይሬክቶሬት በሚወጣ መርሀግብር መሠረት የሚወሰን ይሆናል:: የትራፊክ ተቆጣጣሪው ከመኖሪያ አድራሻው ወደ ስምሪት ቦታው ሲሄድ ከክፍለ ከተማው ውጪ በመንገዱ ላይ የትራፊክ ህግ መተላለፍ ሲፈፀም ቢመለከት ህግ ተላላፊውን በሲስተም ቅጣት በማስተላለፍ ወይም በሲስተም መክፈል የማይቻልበት ሁኔታ ሲያጋጥም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ በመያዝ በአቅራቢያ ለሚገኝ ትራፊክ ተቆጣጣሪ ወይም ለቅ/ጽ/ቤት ያስረክባል::

## 3.8 ለትራፊክ ቁጥጥር ስራ ትኩረት የሚደረግባቸው ቦታዎች

የትራፊክ ቁጥጥር ስራ በማናቸውም የከተማው መንገዶች ላይ በሁሉም የመንገድ ተጠቃሚዎች ማለትም በተሽከርካሪ ወይም በእግረኞች አማካኝነት በሚደረግ እንቅስቃሴ ወይም ዝውውር የሚፈፀምን የመንገድ ትራንስፖርት ህግ መተላለፍ ጥፋት ለማረም በሚመለከታቸው ለስራው በተመደቡ የትራፊክ ተቆጣጣሪዎች አማካኝነት የሚወሰድ እርምጃ ሲሆን የትራፊክ ቁጥጥር ስራ በተለየ ሁኔታ ከዚህ በታች በተገለፁ አካባቢዎች ላይ ትኩረት በማድረግ መስራት አለበት::

## 3.9 ለትራፊክ አደጋ አጋላጭ መንስኤ (Risk Factors) በሆኑ የጥፋት አይነቶች

በአለም የጤና ድርጅት ለትራፊክ አደጋ አጋላጭ መንስኤዎች ወይም የትራፊክ አደጋ ከተደረሰ በኃላ ጉዳት እንዲባባስ የሚያደርጉ ጉዳዮች ከተወሰነው ፍጥነት ወሰን በላይ ማሽከርከር ፣ በአልኮልና ሌሎች አደንዛዥ እፆች ተመርዞ ማሽከርከር ፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ በእጅ ይዞ እያነጋገሩ ማሽከርከር ፣የደህንነት መጠበቂያ ቀበቶና ህፃናት መታቀፊያ ሳያደርጉ ማሽከርከር እንዲሁም የጭንቅላት መከላከያ ቆብ) ሄልሜት) ሳያደርጉ ማሽከርከር ላይ ትኩረት ያደረገ በቴክኖሎጅ ጭምር የተደገፈ ቁጥጥር በማድረግ የትራፊክ አደጋ ተጋላጭነትን መቀነስ ይገባል::

## 3.10 በዋና ዋና እና መጋቢ መንገዶች እንዲሁም መጋጠሚያዎች አካባቢ

የከተማው ተሽከርካሪዎች በዋናነት በዋና ዋና እና መጋቢ መንገዶች ላይ የሚንቀሳቀሱ በመሆኑ በዋናነት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በሚቆጣጠራቸው ዋና ዋና ፣ መጋቢ መንገዶችን እንዲሁም መጋጠሚያዎች ላይ በትራፊክ ቁጥጥር ሠራተኞች አማካይነት የትራፊክ ቁጥጥር እንዲሁም ፍሰት ማሳለጥ ተግባራ የሚከናወኑ ሲሆን የተለየ ትኩረት የሚሹ አካባቢዎችን በመለየት የማእከል የትራፊክ ቁጥጥር ባለሙያዎችም የቁጥጥር ፣ የድጋፍና ክትትል ተግባራትን የሚያከናውኑ ይሆናል::

### 3.11 የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጡ ተርሚናሎችና መጫኛና ማውረጃ(ቤይ) ያለባቸው አካባቢዎች

የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥባቸው ተርሚናሎች ብዛት ያላቸው ተሽከርካሪዎች ተመድበው አገልግሎት የሚሰጡባቸው በመሆኑ በተሽከርካሪ እንቅስቃሴ መብዛት የተነሳ የትራፊክ ፍሰት መጨናነቅ የሚስተዋልባቸው ቦታዎች በመሆናቸው በማእከልና በቅርንጫፍ ትራፊክ ተቆጣጣሪዎች አማካይነት ፍሰት የማሳለጥ ስራዎች እንዲሁም ህግ በሚጥሱት ላይ ቁጥጥር፤ ክትትልና ድጋፍ የሚደረግባቸው ሲሆን ህግንና መመሪያን በማይተገብሩ አሽከርካሪዎች እርምጃ የሚወሰድበት ነው፡፡

በሌላ በኩል በመንገድ ዳር የተገነቡ የአውቶብስና ታክሲ መጫኛና ማውረጃ(ቤይ) ቦታዎች አካባቢ የሚከናወነው ተሳፋሪ የመጫንና የማውረድ ሂደት ለዚህ አላማ ተብሎ በተሰራው ቦታ ላይ ብቻ እንዲከናወን ጥብቅ ቁጥጥር ካልተደረገ ወደ ዋና መንገድ በመግባት የሌሎች ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ በማሰናከል የአካባቢው የትራፊክ ፍሰት እንዲስተጓጎል የሚያደርጉ በመሆኑ በልዩ ትኩረት የመከታተልና ቁጥጥር የማድረግ ስራ መሰራት ይኖርበታል፡፡

በሌላ በኩል በኮሪደር ልማት የለሙ የእግረኛና ተብስክሌት መንገዶች ላይ የተጠናከረ የቁጥጥርና ህግ የማስከበር ስራዎች በመስራት መሰረተ ልማቱ ለታለመለት አላማ እንዲውል የሚደረግ ሲሆን ቅ/ጽ/ቤቶች በእነዚህ ቦታዎች ላይ ልዩ ትኩረትና ስምሪት በመስጠት ተግባራትን እንዲያከናውኑ ይጠበቃል፡፡

### 3.12 በሰዓት የተገደቡ የመንገድ ምልክትና ማመላከቻዎች የተቀመጡበት አካባቢ

እንደየ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በተለይም በስራ መውጫና መግቢያ ሰዓት ወቅት በተሽከርካሪ መብዛት የትራፊክ መጨናነቅ የሚስተዋልባቸውን አካባቢዎች በመለየት ተሽከርካሪዎች ሁሉ ለአጭርም ሆነ ለረጅም ጊዜ እንዳይቆሙ የሚከለከሉባቸው ቦታዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

እነዚህ አካባቢዎች ላይ የተተከሉ የመንገድ ምልክቶችን ያለማቋረጥ የማስከበርና ህግ የሚጥሱት ላይም የትራፊክ ተቆጣጣሪዎች እርምጃ እንዲወስዱና ምልክቶችን በማስከበር የታለመው አላማ ግቡን እንዲመታ የማድረግ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

### 3.13 ለአውቶብስ ብቻ የተለዩ መስመሮችን ማስከበር

በከተማችን ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች ለአውቶብስ ብቻ የተለዩ መስመሮች ተዘጋጅተው ተግባራዊ እየተደረጉ እንደሚገኙ ይታወቃል፡፡ እነዚህ መስመሮች በዋናነት የብዙሀን ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሁም የድንገተኛ ጊዜ አገልግሎት ለሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ብቻ አገልግሎት እንዲሰጡ ታስቦ የተገነቡ ሲሆን ከእነዚህ የተለዩና የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች ውጭ በመስመሩ ላይ የሚንቀሳቀሱ ወይም የሚቆሙ ተሽከርካሪዎች ላይ ትራፊክ ተቆጣጣሪዎች እርምጃ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለአውቶብስ ብቻ በተገነቡ መንገዶች ላይ ከአውቶብስ እና ከድንገተኛ አገልግሎት ከሚሰጡ ተሽከርካሪዎች በስተቀር ሌሎች ተሽከርካሪዎች ገብተው እንዲጠቀሙበት አይፈቀድም፡፡



የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን Addis Ababa Traffic Management Authority

## 3.14 ትምህርትቤቶች እና የኮንስትራክሽን ስራ በሚገኙባቸው አካባቢዎች

ትምህርት ቤቶች በሚገኙባቸው መንገዶች በተለይም በተማሪዎች መውጫና መግቢያ ሰዓቶች በመንገድ ላይ የተቀመጡ የመንገድ ምልክቶችን በመጣስ ወይም ሌላ ተሽከርካሪን ደርቦ በማቆም የአካባቢው የትራፊክ እንቅስቃሴ እንዲሰናከል ስለሚያደርጉ በልዩ ትኩረት ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

የኮንስትራክሽን ስራ የሚካሄድባቸው አካባቢዎች ከፍተኛ የሆነ የከባድ ተሽከርካሪዎች እና የእግረኞች እንቅስቃሴ የሚበዛበት በመሆኑ ለትራፊክ ፍሰት መስተጓጎል ፣ በጫኑት ጭነት ወይም በጎማቸው መንገድ እንዲበላሽ የሚያደርጉበት አልፎ ተርፎም ለትራፊክ አደጋ ተጋላጭ ሁኔታዎች በሚፈጠሩበት በመሆኑ በልዩ ትኩረት የትራፊክ ቁጥጥር እና ፍሰት የማሳለጥ ተግባራት ይከናወኑበታል፡፡

## 3.15 እግረኞች የሚበዙባቸው አካባቢዎች

በከተማችን በሚደርሱ የትራፊክ አደጋዎች አብዛኛዎቹ የአደጋው ሰለባዎች እግረኞች እንደመሆናቸው ይህን ለመቀነስ የሚያስችሉ ሰስራዎችን መስራት ይገባል፡፡በዚህ መሠረት በእግረኞች ላይ አደጋ በብዛት የሚደርሱባቸውን ቦታዎች በጥናት በመለየት መሠረተ ልማት የተሟላባቸው መሆኑን በማረጋገጥ ተገቢውን የመንገድ አጠቃቀም በማይከተሉ እግረኞች ላይ ተከታታይነት ያለው ቁጥጥር በማድረግ በጊዜ ሂደት ተገቢውን የመንገድ ስነ ስርዓት ተከትሎ መንገዶችን መጠቀምን በከተማችን በህል ማድረግ ስለሚገባ የእግረኞች ቁጥጥር አንደኛው የትኩረት አቅጣጫ ችን መሆን ይገባዋል፡፡

## 3.16 ከፍጥነት ወሰን በላይ ማሽከርከር እና አልኮል ጠጥቶ ማሽከርከር ቁጥጥር የሚካሄድባቸው ቦታዎች

1. ከፍጥነት ወሰን በላይ ማሽከርከርን ለመከላከል የሚደረግ ቁጥጥር የሚካሄድባቸው ቦታዎች የሚመረጡት ተደጋጋሚ የትራፊክ ግጭት ተከስቶ ሞትና ከባድ የአካል ጉዳት የሚደርስባቸው ቦታዎች ላይ ይሆናል፡፡ የቁጥጥር ቦታዎችን ለመወሰን ከፖሊስ የትራፊክ ግጭት ሪፖርት በመውሰድ በስራ ክፍል ደረጃ የጋራ ማድረግ ማጽደቅና ለማዕከል ማሳወቅ ይገባል፡፡በተመረጡ ቦታዎች ላይ ተከታታይ በራዳር የተደገፈ ቁጥጥር ቢደረግም በቦታው የሚደርሰው የትራፊክ ግጭት የማይቀንስ ከሆነ ሌሎች እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለማዕከል ማሳወቅ ይገባል፡፡በፍጥነት ቁጥጥር ወቅት በራዳር የተመዘገቡ መረጃዎች በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት ተመዝግበው መያዝ ይገባቸዋል፡፡

   አልኮል ጠጥቶ ማሽከርከርን ለመከላከል የሚደረግ ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ቦታዎች ለዚህ ተጋላጭ የሆኑ ቦታውን በቅድሚያ በመለየትና በመወሰን ይሆናል፡፡ሰክሮ በማሽከርከር የተገኘ አሽከርካሪ ሌላ ብቁ የሆነ አሽከርካሪ ተሽከርካሪውን እንዲያሽከረክርለት ካላደረገ በስተቀር ትራፊክ ተቆጣጣሪው ተሽርካሪውን ለአስራ ሁለት /12/ ሰዓታት ይዞ ማቆየት የሚችል ሲሆን በትራፊክ ተቆጣጣሪ የተያዘ ተሽከርካሪ ደህንነቱ ወደ ማያሰጋ ቦታ ተወስዶ እንዲቆይ መደረግ ይኖርበታል፡፡የተጠቀሰው ጊዜ ሲያልፍ ተሽከርካሪውን ለመረከብ የቀረበው ሰው መስከሩ የተረጋገጠው አሽከርካሪ ከሆነ በድጋሚ ምርመራ ተደርጎለት አለመስከሩ ሳይረጋገጥ

ተሽከርካሪውን እንዲወስድ መደረግ የለበትም፡፡ ተሽከርካሪውን ደህንነቱ ወደ ማያሰጋ ቦታ ለማገገዋዝና ለጥበቃ ወጣውን ወጪ የተሽከርካሪው ባለቤት ይሸፍናል፡፡

2. ከፍጥነት ወሰን በላይ ማሽከርከርንም ሆነ አልኮል ጠጥቶ ማሽከርከርን ለመከላከል የሚደረግ ቁጥጥር ወቅት ከ8 እስከ 10 የሚሆኑ የተሟላ የደንብ ልብስና አንፀባራቂ ጃኬት የለበሱ ተቆጣጣሪዎች መሳተፍ የሞኖርባቸው ሲሆን የቁጥጥር ቦታው ተሽከርካሪዎችን ለማስቀም በሚያመች መልኩ ከ8 እስከ 10 በሆኑ ኮኖች ተከልሎ መዘጋጀትና ደህንነቱ የተረጋገጠ መሆን ይኖርበታል፡፡በኦፕሬሽኑ የሚሳተፉ ሁሉም ተቆጣጣሪዎች ስራው ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ በንቃትና ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ መሳተፉ ይኖርባቸዋል፡፡በአንድ ጊዜ የሚደረግ ኦፕሬሽን እስከ 2 ሰዓት ለሚደርስ ሰአት መከናወን ይኖርበታል፡፡ፍተሻ ጣቢያዎች ለህግ አስከባሪ አካላት ተሽከርካሪዎች እና ለምርመራ ተግባር ለሚቆሙ ተሽከርካሪዎች መቆሚያ ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሁም የክስ ቻርጅ ለመፃፍ በቂ ቦታ ሊኖር ይገባል።

## 3.17 የትራፊክ ቁጥጥር የሚካሄድባቸው ቀናትና ሰዓቶች

### 3.17.1 የትራፊክ ቁጥጥር የሚካሄድባቸው ቀናቶች

የቅርንጫፍ ጽ/ቤት የትራፊክ ቁጥጥር ሠራተኞች መደበኛ የስራ ቀናት ከሰኞ እስከ ቅዳሜ በየዕለቱ በመደበኛነት የትራፊክ ቁጥጥር ስራው ለተከታታይ 6 ቀናት የሚከናወን ሲሆን እሁድ እና በበዓላት ቀናት የትራፊክ ቁጥጥር ስራው አይካሄድም፡፡ ነገር ግን በልዩ ሁኔታ እንደ አስፈላጊነቱ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ በማእከልና በቅርንጫፍ ጽ/ቤት እውቅና የትራፊክ ቁጥጥሩ የሚካሔድ ይሆናል፡፡

### 3.17.2 የትራፊክ ቁጥጥር የሚካሄድባቸው ሠዓቶች

የቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሳይት አስተባባሪዎችና የትራፊክ ቁጥጥር ሠራተኞች መደበኛ የትራፊክ ቁጥጥር ስራው ወጥነት ባለው ሁኔታ በዋናነት በሁለት ፈረቃ ይከናወናል፡፡ የመጀመሪያው ፈረቃ ከጠዋቱ 12:30 ሰዓት ጀምሮ እስከ 7:00 ሰዓት ድረስ የሚካሄድ ሲሆን የሁለተኛው ፈረቃ የትራፊክ ቁጥጥር ስራ ከቀኑ 7:00 እስከ ምሽቱ 1:30 በመደበኛነት ከላይ በተጠቀሱት ቀናቶች ወጥ በሆነ ሁኔታ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንደየ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ የትራፊክ ቁጥጥር ስራ የሚካሄድባቸውን ሰዓቶች በሳምንት ከ39 ሰዓት እንዳይበልጥ በማድረግ የማሽጋሸግ ስራ ሊሰሩ ይችላሉ፡፡

### 3.17.3 የትርፍ ሰዓት ስራን በተመለከተ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ ባወጣው መመሪያ መሠረት የመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበርና ቁጥጥር ሠራተኞች ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጪ በጠዋትና ማታ እንዲሁም ስራ ዝግ በሆነባቸው ቀናት ስራ እንዲገቡና እንዲሰሩ ከተደረገ በትርፍ ሰዓት ስራ ይያዛል፡፡ ከእነዚህ ስራ መደቦች ውጭ በትርፍ ሰዓት ስራ ሠራተኞችን ለማሰማራት በቅድሚያ ለባለስልጣኑ ሰው ህብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

በማሳወቅና የዳይሬክቶሬቱን አውንታን ማግኘት ይጠይቃል፡፡ከሰው ኃብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እውቅና ውጭ ለተሰራ የትርፍ ሰዓት ስራ ክፍያ አይፈጸምም፡፡

### 3.18 የትራፊክ ቁጥጥር የሚካሄድባቸው አካላት

በአዲስ አበባ ከተማ ክልል ውስጥ በሚንቀሳቀሱ እና የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ህግ በሚተላለፉ ማናቸውም አይነት ተሽከርካሪዎች እና እግረኞች ላይ ቁጥጥር የሚደረግ ሲሆን የሞተር ብስክሌት እና የጭነት ተሽከርካሪዎች ላይ ከእንቅስቃሴ ገደብ ጋር በተያያዘ ልዩ ቁጥጥር በማድረግ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፡፡

### 3.19 የትራፊክ ቁጥጥር የስራ ስምሪት እና ፈረቃ

የትራፊክ ቁጥጥር ሠራተኞች ውጤታማ ስራ ለመስራት ሲባል በየወሩ የስራ ቦታቸው ወይም ሳይት ወይም መስመር የሚለዋወጥበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን አንድ የቁጥጥር ሠራተኛ በተመደበበት ቦታ ወይም ሳይት ከአንድ ወር በላይ እንዲቆይ መደረግ የለበትም፡፡ ይህ ማለት ቀጣዩ ስምሪት ሁኔታ ሲዘጋጅ በሌላ የዙር ወቅት ተመልሶ ሊመደብ አይችልም ማለት እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡ወርሀዊ ስራ ቦታ ድልድል በሚደረግበት ወቅት አሳማኝና በቂ ምክንያት ያላቸው ተቆጣጣሪዎች ሲያጋጥሙ በሌሎች ሠራተኞች ላይ ቅሬታ በማይፈጥር መልኩ በልዩ ሁኔታ ሊስተናገዱ የሚችሉበትን መንገድ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ኃላፊ ሊወስን ይችላል፡፡

የትራፊክ ቁጥጥር ሠራተኞች ስራ ሁኔታ በፈረቃ በሚቀያየር መርሀ ግብር የሚመራ እንደመሆኑ መጠን አንድ የትራፊክ ቁጥጥር ባለሙያ በወሩ ውስጥ ለ15 የስራ ቀናት በጠዋቱ መርሀ ግብር ለትራፊክ ቁጥጥር ስራ ከተሰማራ ለቀጣዩቹ 15 ቀናት በከሰአት በኃላ መርሀ ግብር እንዲሰማራ ይደረጋል፡፡ የትራፊክ ተቆጣጣሪዎች በሳይት ምደባ ሲደረግ አንድ የትራፊክ ተቆጣጣሪ ቢያንስ በ500 ሜትር ራድየስ ውስጥ እንዲሸፍን ተደርጎ ምድባ ይሰጠዋል፡፡አንድ የቡድን አስተባባሪ ከ10 የማይበልጡ የትራፊክ ቁጥጥር ሠራተኞችን በስሩ ያስተባብራል፡፡በሸፍት ሱፐርቫይዘር በሚወጣው ድልድል መሠረት በተደለደሉበት መንገዶች እንደ መንገዱ ሁኔታ እና የሚሸፍነው ስፋት በቂ የትራፊክ ቁጥጥር ሠራተኞችን ይመድባል፡፡

### 3.20 በመንገድ ትራንስፖርት ህግ ተላላፊዎች ላይ እርምጃ ስለመውሰድ

የትራፊክ ተቆጣጣሪው የመንገድ ትራንስፖርት ህግ የተላለፈ አሽከርካሪ ሲያጋጥመው በቅድሚያ የተሽከርካሪ ማስቆሚያ ምልክት(ስቶፐር) በማሳየት የመንገዱን ጠርዝ በመያዝ ተሽከርካሪውን እንዲያቆም አሽከርካሪውን ያዘዋል፡፡ተሽከርካሪውን ሲያስቆም የትራፊክ እንቅስቃሴውን በማያውክ መልኩ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ እንዲቆም በታዘዘው መሰረት ለቆመ ተሽከርካሪ በትክክል መቆሙን ካረጋገጠ በኃላ ወደ አሽከርካሪው በመጠጋትና ሰላምታ በመስጠት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲሰጠው ይጠይቃል፡፡

የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተቀበለ ተቆጣጣሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ተሽከርካሪውን በወቅቱ የያዘው አሽከርካሪ የራሱ መሆኑንና ጊዜው ያለለፈበት መሆኑን በማረጋገጥ የተላለፈውን የትራፊክ ህግ

በማስረዳት የመንገዱን ጠርዝ በመያዝ የትራፊክ ቅጣት በተዘጋጀው ታብሌት በመጠቀም በሲስተም ኤሌክትሮኒክ ቅጣት እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡

የትራፊክ ህግ የተላለፈው አሽከርካሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያልያዘ ከሆነ ወይም ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም በቅጣት ወረቀት እያሽከረከረ ከሆነ ወይም የደንብ መተላለፍ ጥፋት ፈጽሞ በቦታው ካልተገኘ የተሽከርካሪውን ሰሌዳ በመጠቀም ቅጣት ማስተላለፍ ይገባል፡፡

ደንብ ተላላፊው የአሽከርካሪ ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም የተሽከርካሪ ሰሌዳ በሲስተም ካልተገኘ ለመጀመሪያ ጊዜ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በመቀበል ወይም ሰሌዳ በመፍታት የአድራሻ ማሳወቂያ በመስጠት በቢሮ ተመዝግቦ ቅጣቱን በሲስተም እንዲፈጽም መደረግ ይኖርበታል፡፡

የተሽከርካሪ ሰሌዳ የግድ መፍታት አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ወቅት የተሽከርካሪውን ሞተር እንዲያጠፋ በማድረግ የተሽከርካሪውን የፊት ሰሌዳ በመፍታት የአድራሻ ማሳወቂያ መስጠት ይኖርበታል፡፡ በዚህ ሂደት በቅድሚያ እንዲቆም ሲጠየቅ ለመቆም ፈቃደኛ ያልሆነ አሽከርካሪ ሲያጋጥም የተሽከርካሪዎን ሰሌዳ በሲስተሙ ተፈላጊ ተሽከርካሪ ሰሌዳ መመዝገቢያ ላይ እንዲመዘገብ መረጃውን በመያዝ ለቅርብ ሃላፊ ያስተላልፋል፡፡

## 3.21 የተሽከርካሪ ሰሌዳ ስለመፍታት

የትራፊክ ተቆጣጣሪው በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህጎች መተላለፍ ምክንያት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ወደ መፍታት ሊሸጋገር የሚገባው በዚህ ማንዋል በግልጽ በተፈቀደው አግባብ በዲጅታል ኢንፎርስምንት ማኔጅመንት ሲስተም አማካኝነት ቅጣት ለመክፈል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ መረጃ በሲስተም ካልተገኘ ወይም አሽከርካሪው የያዘው መንጃ ፈቃድ የውጪ ሀገር መንጃ ፈቃድ ከሆነ ብቻ ይሆናል፡፡ እንደዚህ በሆነ ጊዜ የትራፊክ ተቆጣጣሪው የፊት ሰሌዳ ብቻ በመፍታት ይዛል፡፡ በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን የመንገድ ትራንስፖርት ህግ ጥፋትን ለማስፈፀም የኃላ ሰሌዳ ወይም የፊት እና የኃላ ሰሌዳ በአንድ ላይ ፈቶ መያዝ አይፈቀድም፡፡

የተሽከርካሪው ሰሌዳ ከተፈታ በኃላ የትራፊክ ተቆጣጣሪው ከቦታው ሳይርቅ አሽከርካሪው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይዞ ከቀረበ ሰሌዳው በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ እንዲቀየር ተደርጎ የትራፊክ ቅጣቱን በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ እንዲፈፅም ይደረጋል፡፡ ከተሽከርካሪ የተፈታ ሰሌዳ በጥንቃቄ እንዳይሰበር ሆኖ ሳይተጣጠፍ መያዝ አለበት፡፡

ሰሌዳው ሲፈታ የተገኙ ማሰሪያ ቡለኖች በነበሩበት ቦታ በጥንቃቄ ተመልሰው እንዲታሰሩ መደረግ ያለበት ሲሆን ሰሌዳውን ለመፍታት አስቸጋሪ ከሆኑ የተሽከርካሪውን መረጃ በመያዝ ለአስተባባሪው ሪፖርት በማድረግ የተሽከርካሪው ባለቤት በሌላ መንገድ እንዲቀርብ ከማድረግ ባለፈ ሰሌዳውን ለመገንጠል ጥረት ማድረግ አይፈቀድም፡፡

## 3.22 የቅጣት አዘገጃጀት

የትራፊክ ተቆጣጣሪው የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላልፈው በተገኙ አሽከካሪዎች ላይ የሚፈጸመው ቅጣት ሂደቱን የሚያስተጓጉል ነገር ካልተፈጠረ በስተቀር በከፍተኛ ጥንቃቄ በ5 ደቂቃ ውስጥ አጠናቆ

ለአሽከርካሪው ኤሌክትሮኒክስ የቅጣት መረጃው እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፡፡ ትራፊክ ተቆጣጣሪው ለደንብ ተላላፊው በሲስተም ያስተላለፈው ቅጣት በእጅ ስልኩ ወይም የተመዘገበው ስልክ የሌላ ሰው ከሆነ ለትክክለኛው ሰው መድረሱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ የትራፊክ ተቆጣጣሪው የደንብ ተላላፊውን መረጃ በሲስተም በሚሞላበት ወቅት ስህተት እንዳይፈጠር ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡የተሞላውን መረጃ ትክክለኛነት ሳያረጋግጥ ቅጣቱ እንዲተላለፍ ማድረግ የለበትም፡፡

የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ህግ በመተላለፍ ምክንያት በሲስተም ኤሌክትሮኒክ ቅጣት የሚተላለፍላቸው ከመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 557/2016 ላይ የተቀመጡ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች ብቻ ሲሆን ሌሎች በአዋጅ ወይም በመመሪያ የተጣሉ ቅጣቶች በባለስልጣኑ በልዩ ሁኔታ በሚዘጋጁ ቅፆች መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ የተሽከርካሪ አመታዊ ምርመራ አድርገው ሰርተፊኬቱን ሳይለጥፉ የሚያሽከረክሩ፣ የሞተር ብስክሌት ፈቃድና ቁጥጥር፣የጭነት ተሽከርካሪዎች ፈቃድና ቁጥር፣ ወዘተ በመተላለፍ ሲያሽከረክሩ የተገኙ ተሽከርካሪዎችን ይመለከታል፡፡

## 3.23 የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ ስለሚመለስበት ሁኔታ

የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ህጎችን በመተላለፍ ቅጣት የተጣለበት አሽከርካሪ በትራፊክ ተቆጣጣሪው የተያዘበት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሊመለስ የሚችለው አሽከርካሪው ቅጣቱን ፈፅሞ ሲቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡

አንድ ጊዜ በደንብ መተላለፍ ጥፋት ምክንያት ተይዞ ገቢ የተደረገ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ ቅጣቱ ሳይፈፀም ለአሽከርካሪው ተመላሽ ሊሆን የሚችለው የተጣለው ቅጣት አግባብ ባለው ስራ ኃላፊ ሲሻር ወይም ሲታረም ብቻ ይሆናል፡፡

የትራፊክ ቅጣት መፈፀሙን በማረጋገጥ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ በመመለስ ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች ደንብ ተላላፊው ይዞት የቀረበው ቅጣቱን ስለመክፈሉ የሚያስረደዳው ደረሰኝ በትክክል በቅጣት ደረሰኙ ላይ የተጣለውን ቅጣት ስለመፈፀሙ፣ቅጣቱ በደንብ ተላላፊው ስምና አሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ቁጥር የተከፈለ መሆኑን በማረጋገጥ፣ ቅጣቱ የተፈፀመው ባለስልጣኑ ውክልና በሰጣቸው ባንኮች በሲስተም መሠረት መሆኑን፣ በደንብ ተላላፊው ላይ የተጣለው ቅጣት ተደራራቢ ሲሆን ሁሉንም ቅጣቶች ክፍሎ ሲቀርብ እንዲሁም የትራፊክ ቅጣቱ ያለቅጣት መክፈያ ጊዜው ከማለፉ በፊት መሆኑን ወይም የክፍያ ጊዜው በመዘግየቱ በቅጣት/ወለድ ጨምሮ መክፈል የሚገባው አሽከርካሪ ከሆነ ቅጣቱን/ወለዱን ጨምሮ መክፈሉን በማረጋገጥ መሆን ይኖርበታል፡፡

የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ የሚመለሰው ለአሽከርካሪው ለራሱ ወይም ህጋዊ ወኪል እንዲሁም ሰሌዳ የሚመለሰው ሰሌዳው ሲፈታ ተሽከርካሪውን ሲያሽከረክር ለነበረው አሽከርካሪ ወይም ሊብሬ ይዞ ለሚቀርብ የተሽከርካሪ ባለቤት ወይም ህጋዊ ወኪል ብቻ በተዘጋጀው ቅፅ በማስፈረም ይሆናል፡፡

### 3.24 ለደንብ ተላላፊዎች በቂ መረጃ ስለመስጠት

የትራፊክ ተቆጣጣሪው በትራፊክ ህግ መተላለፍ ጥፋት ቅጣት በሲስተም ጽሮ ለሰጠው አሽከርካሪ ቅጣቱን የት መፈፀም እንደሚችል (ባለስልጣኑ ቅጣት እንዲሰበስቡ ስልጣን በሰጣቸውን ባንኮች) መክፈል እንዳለበት ፣ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ወይም ሰሌዳውን ከየት መውሰድ እንደሚችል እንዲሁም በተጣለበት ቅጣት ቅሬታ ማቅረብ ከፈለገ ለማን ማቅረብ እንደሚችል በግልፅ ማስረዳት ወይም ጽሮ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

እነዚህን መረጃዎች ለመስጠት አሽከርካሪው በቦታው ባልተገኘ ጊዜ ወይም አሽከርካሪው እነዚህን መረጃዎች ለመውሰድ ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ በትዕግስት መረጃውን በመፃፍ በተሽከርካሪው የዝናብ መጥረጊያ ወይም በሌላ አመቺ በሆነ ቦታ በማስቀመጥ መሄድ ይኖርበታል፡፡

የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ የተያዘበትን አሽከርካሪ የተወሰዱበትን መረጃዎች ከየት መውሰድ ወይም መጠየቅ እንዳለበት ሳያሳውቁ መሄድ በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም፡፡

ሰሌዳ ለተፈታባቸው አሽከርካሪዎች የሚሰጠው የአድራሻ ማሳወቂያ ማስረጃ ፣ የደንብ መተላለፍ ጥፋት የተፈፀመበትን ቀን፣ የተሽከርካሪውን ሰሌዳ ቁጥር፣ የተሽከርካሪውን አይነት፣ የተፈፀመው ጥፋት አይነት፣ የተቆጣጣሪውን ስም እና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የሚገኝበትን አድራሻ እና የሚሰራ ስልክ ቁጥር እንዲሁም በተሰጠው ማስረጃ በመጠቀም አሽከርካሪው ለምን ያህል ሰዓት ማሽከርከር እንደሚፈቀድለት የሚገልፅ ጽሁፍ ያለበት ይሆናል፡፡

የተሽከርካሪው ሰሌዳ የተፈታበት አሽከርካሪ በተሰጠው ማስረጃ በመጠቀም ተሽከርካሪ እንዲያሽከረክር የሚፈቀድለት ለ12 ሰዓታት ብቻ ይሆናል፡፡ ይህም ጊዜ የሚሰጠው ተሽከርካሪውን ከቆመበት ቦታ ወደ ቤቱ ወይም ወደተዘጋጀለት ማቆሚያ ቦታ ለመማድረስ ወይም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫው ፈቃዱን ይዞ በመቅረብ ሰሌዳውን ለማስለቀቅ ሰሌዳው ወደተያዘበት የትራፊክ ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት ለመድረስ ብቻ ይሆናል፡፡

### 3.25 የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ ስለማስረከብ

ትራፊክ ተቆጣጣሪው ከትራፊክ ህግ ተላላፊው የተቀበለውን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ከተሽከርካሪ የተፈታውን ሰሌዳ ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ካልተፈጠረ በስተቀር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን በተቀበለበት ወይም ሰሌዳውን በፈታበት ቀን ለቡድን አስተባባሪው በማስፈረም ማስረከብ ይኖርበታል፡፡የቡድን አስተባባሪው ከትራፊክ ተቆጣጣሪው የተረከበውን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ እጅግ ቢዘገይ ከ12 ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለሚመለከተው የስራ ክፍል አስፈርሞ ማስረከብ አለበት፡፡

### 3.26 የስራ መግቢያና መውጫ ሰዓት

የትራፊክ ተቆጣጣሪው መደበኛ የስራ ሰዓት ከሚጀምርበት ሰዓት 15 ደቂቃ አስቀድሞ በስራ ቦታው በመገኘት ለስራ ዝግጁ መሆን ይጠበቅበታል፡፡መደበኛ የስራ ሰዓቱን ካጠናቀቀ በኃላ ስራ ቦታውን ከመልቀቁ በፊት ቢያንስ ለ15 ደቂቃ የውሎውን ሁኔታ በመመዝገብና አስፈላጊ ቁሳቁሶቹን መኖራቸውን በማረጋገጥ ስራ ቦታውን ለቆ ይሄዳል፡፡

### 3.27 በቁጥጥር ወቅት ተገቢውን ጥንቃቄ ስለማድረግ

የትራፊክ ተቆጣጣሪዎች የቁጥጥር ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት ሙሉ ትኩረታቸውን በስራው ላይ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም የትራፊክ ተቆጣጣሪዎች በተመደቡበት የስራ ቦታ ላይ ያለውን የትራፊክ እንቅስቃሴና የደንብ መተላለፍ ሁኔታዎች በማስተዋል ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው ማለት ነው፡፡ትኩረታቸውን ከሚስቡ ማናቸውም ሁኔታዎችና ድርጊቶች ራሳቸውን በማራቅ ተግባራቸውን ማከናወን ሚገባቸው ሲሆን ተገቢወን ትኩረት ማድረግ የትራፊክ ተቆጣጣሪዎች ራሳቸውን ከትራፊክ አደጋ እና ሌሎች እክሎች መጠበቅን ሁሉ የሚያተቃልል ነው፡፡

### 3.28 የትራፊክ ቁጥጥር ስራን ባስናከሉ ደንብ ተላላፊዎች የሚጣል ቅጣት

የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ህጎች በመተላለፍ ቅጣት የተጣለበት አሽከርካሪ ቅጣቱን በመቃወም በትራፊክ ተቆጣጣሪው ላይ ለሚያሳየው ተግባር የዲሲፕሊን ቅጣት የሚጣለው ድርጊቱ ስለመፈፀሙ በማስረጃ ሲረጋገጥ መሆን ይኖርበታል፡፡በዚህ ሂደት የትራፊክ ተቆጣጣሪው ሚና መረጃውን በዝርዝር ለአስተባባሪው ማሳወቅ ብቻ ይሆናል፡፡የትራፊክ ቁጥጥር የቡድን አስተባባሪው አሽከርካሪው የፈፀመው ድርጊት ለተጨማሪ ቅጣት የሚዳርገው መሆን አለመሆኑን በማጣራት አስተያየቱን በመጨመር ለትራፊክ ቁጥጥር ቡድን መሪ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡የውሳኔ ሀሳብ የቀረበለት የትራፊክ ቁጥጥር ቡድን መሪ ጉዳዩን በመመርመር ቅጣት መጣል አለበት ወይም የለበትም የሚለውን ይወስናል፡፡የትራፊክ ደንብ ተላላፊው የፈፀመው ድርጊት በገንዘብ ቅጣት ከማለፍ ይልቅ ጉዳዩ በወንጀል መያዝ ካለበት አስፈላጊውን መረጃና ማስረጃ በመያዝ ለህግ አገልግሎት ቡድን ያስተላልፋል፡፡የህግ አገልግሎት ቡድን ጉዳዩን ተቀብሎ ለወንጀል ምርመራ ለፖሊስ ካስተላለፈና አሽከርካሪው ከፖሊስ ቀርቦ ቃሉን ከሰጠ በኃላ የተያዘበት መረጃ እንዲለቀቅለት ይደረጋል፡፡ደንብ ተላላፊው በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን በፈፀመው ድርጊት በወንጀልም በገንዘብም በአንድላይ ተጠያቂ ሊሆን አይችልም፡፡

### 3.29 የትራፊክ አደጋ ሁኔታ አመዘጋገብ

የትራፊክ ተቆጣጣሪው የትራፊክ ቁጥጥር ስራውን ሲያከናውን ቀላል የትራፊክ አደጋ ቢከሰት እና በአካባቢው የትራፊክ ፖሊስ ከሌለ በራሱ ተገቢውን ምልክት በማድረግ እና የአሽከርካሪዎችን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በመቀበል ተሽከርካሪው እንዲነሳ በማድረግ የትራፊክ ፍሰቱን ወደነበረበት ሁኔታ መመለስ ይጠበቅበታል፡፡ ይሁን እንጅ የደረሰው የትራፊክ አደጋ ከባድ ከሆነ ወይም የደረሰው አደጋ ከተቆጣጣሪው አቅም በላይ በመሆኑ ችግሩ በእርሱ የማይፈታ መሆኑን ሲረዳ ወድውኑ የአሽከርካሪዎችን አሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ

በመቀበልና በመያዝ የደረሰውን ትራፊክ አደጋ ለቡድን አስተባባሪው በማሳወቅ የትራፊክ ፖሊስ እንዲመጣ መረጃ ያስተላልፋል፡፡የአደጋውን ሁኔታ በያዘው ታብሌት በመጠቀም በፎግራፍና በፊዲዮ መረጃ መያዝ ይኖርበታል፡፡

የትራፊክ አደጋን በተመለከተ የትራፊክ ተቆጣጣሪውን አደጋ ያደረሱ ተሽከርካሪዎችን መረጃ ከመያዝ ጋር በተያዘ ማናቸውንም አይነት የትራፊክ አደጋ ያደረሱ ማለትም ከተሽከርካሪ ለተሽከርካሪ ፣ ተሽከርካሪ ከግኡዝ ነገር ጋር ወይም ተሽከርካሪ በሰው አካልና ህይወት ላይ አደጋ ባደረሰና የፀጥታ አካላት በሌሉባቸው ቦታዎች ሁሉ መረጃው መያዝ ይኖርበታል፡፡

በትራፊክ አደጋ ወቅት የትራፊክ አደጋ ያደረሱ አሽከርካሪዎችን ስምና አድራሻ፣የአሽከርከሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ቁጥር፣ የተሰጠበትን ቦታ፣ የአሽከርካሪውን ስልክ ቁጥር፣ኢንሹራንስ የተገባበትን ኩባንያ ስም፣ ተሽከርካሪውን ሰሌዳ ቁጥር፣ አደጋው የደረሰበን ቦታ፣አደጋ የደረሰበት ቀንና ሰዓት በአግባቡ መዝግቦ መያዝ ከትራፊክ ተቆጣጣሪው ይጠበቃል፡፡የደረሰውን የትራፊክ አደጋ የትራፊክ ተቆጣጣሪው ራሱ ወይም ያደጋውን ያደረሱ አሽከርካሪዎች ተሽከርካሪው ከመነሳቱ በፊት በሞባይል ፎቶ ምስሉን ማስቀረት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 3.30 የትራፊክ ፍሰትን የማስተናበር ስራ

የትራፊክ ተቆጣጣሪው በተመደበበት አካባቢ የሚኖረውን የትራፊክ እንቅስቃሴ በንቃት መከታተል ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህን ኃላፊነት በሚወጣበት ወቅት የትራፊክ አደጋ እንዳይከሰት ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል ለዚህም በትራፊክ ተቆጣጣሪው ለአሽከርካሪው የሚሰጡ ትእዛዞች ግልፅ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡የትራፊክ ማስተናበር ስራዎች የሚከናወኑት ሁለት እና ከዛ በላይ በሆኑ ትራፊክ ተቆጣጣሪዎች በሆነ ጊዜ እርስ በእርሳቸው በተገቢው ሁኔታ መናበብ እና አደጋ እንዳይከሰት ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው፡፡በተለይም በስራ መግቢያና መውጫ ሰዓት የትራፊክ ተቆጣጣሪዎች ሁሉ የትራፊክ ፍሰትን በማሳለጥ ተግባር ላት ትኩረት ሰጥተው መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 3.31 የስራ ቁሳቁሶች እና ከህግ ተላላፊዎች የተረከቡዋቸውን መረጃዎች በአግባቡ ስለመያዝ

የትራፊክ ተቆጣጣሪው ለመስክ ስራ ከኤጀንሲው የተረከባቸውን ንብረቶች/የስራ ቁሳቁሶች በአግባቡ በመያዝ ሊጠቀምባቸው ይገባል። ለመስክ ስራ ከባለስልጣኑ የተረከባቸው ንብረቶች ቢጠፉ ሳይዘገይ ማሳወቅ አለበት፡፡ ማንኛውም ትራፊክ ተቆጣጣሪ ለስራው ማከናኛ በተሰጡት መሳሪዎች እና መገልገያዎች ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ጥፋት ወይም ጉዳት ቢያደርስ በእዳ ተጠያቂ እንደሚሆን ተገንዝቦ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

የትራፊክ ተቆጣጣሪው በተመሳሳይ በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላላፊዎች ቅጣት ለማስፈፀም የተረከባቸውን አሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እና ሰሌዳዎች በአግባቡና በጥንቃቄ ጠብቆ በመያዝ አግባብ ላለው አካል በወቅቱ በማስረከብ ሀላፊነቱን መወጣት ይኖርበታል፡፡

### 3.31.1 የትራፊክ ቁጥጥር ቁሳቁሶች አያያዝና አጠቃቀም

በባለስልጣኑ የተሰማራ የትራፊክ ተቆጣጣሪ ለቁጥጥር ስራው አጋዥ የሆኑ መሳሪያዎችን ማለትም የዲጅታል ቅጣት ማስፈጸሚያ ታብሌት ፣ የቁም ታፔላ (Stoper)፤ ፊሽካ፤ የደንብ መተላለፍያ ቦርሳ፤ ልዩ ልዩ የመረጃ መመዝገቢያና ማጠናቀሪያ ቅጻ ቅጾችና ሰነዶችን፤ የዝናብ ልብስ፤ እስክርቢቶና ጃንጥላ የመሳሰሉትን መሳሪያዎች በተገቢው ሁኔታ በማሟላት በተመደበበት ቦታ ይዞ መገኘት አለበት፡፡

የትራፊክ ቁጥጥር የሚያከናውን ተቆጣጣሪ ሰራተኛ የቅጣት መስጫ ሰነዶችን በወቅቱ ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ ጥፋቱ በተፈጸመበት ቦታ፣ ጊዜና ሠዓት በወቅቱ በመሙላት የቅጣት ሰነዱን በአግባቡ ማስተላለፍ ይኖርበታል፡፡

የትራፊክ ተቆጣጣሪው የትራፊክ ቁጥጥር ስራውን አገልግሎት እንዲያከናውን በባለስልጣኑ የተሰጠውን የቁም ታፔላ (Stoper) የቁጥጥር ስራውን እንዲካሄድ በተመደበበት ስራ ቦታና በመደበኛ የስራ ጊዜ ብቻ መጠቀም ይኖርበታል፡፡

የትራፊክ ተቆጣጣሪው ለስራው አገልግሎት የተረከበውን አንጸባራቂ ጃኬትና የቁም ታፔላ (Stoper) በማናቸውም ጊዜና ቦታ ለማይገባ ሌላ ዓላማ እንዲውል እንዲሁም ለሌላ 3ኛ ወገን ወይም አካል አሳልፎ መስጠት የለበትም፡፡

በተመሳሳይ የትራፊክ ተቆጣጣሪው በቁጥጥር ወቅት በሚመደብበት የስራ ቦታ በየዕለቱ መረጃዎችን የሚመዘግብበትንና የሚያጠናቅርበትን ሰነዶች እና ሌሎች ቁሳቁሶች በተገቢው ሁኔታ በጥንቃቄ ይዞ መገኘት ይኖርበታል፡፡

### 3.31.2 የትራፊክ ቁጥጥር የደንብ ልብስ አጠቃቀም

ባለስልጣኑ በመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበርና ቁጥጥር ስራ መደቦች ለተመደቡ መደበኛ ሠራተኞች የደንብ ልብስ ያቀርባል፡፡ የመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበርና ቁጥጥር ሠራተኞች ፣ የቡድን አስተባባሪዎች ፣ ቡድን መሪዎችና ዳይሬክተሮች በተመደቡበት ሳይት የደንብ ልብሳቸውን አሟልው ለብሰው በመገኘት ስራቸውን በአግባቡ ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡ የባለስልጣኑ ተቆጣጣሪ ሠራተኞች የደንብ ልብሱን በመልበስ ለቁጥጥር ስራው በተመደቡባቸው ሳይት ወይም መንገዶች ላይ በመገኘት ዕለታዊ የትራፊክ ቁጥጥር ስራውን ያከናውናል፡፡ በማናቸውም መልኩ ለስራ የተሰጠውን የደንብ ልብስ ሳይለብሱ የቁጥጥር ስራ ማከናወን የሌለባቸው ሲሆን የደንብ ልብሳቸውን ለ3ኛ ወገን አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ነው፡፡የትራፊክ ተቆጣጣሪ ሠራተኛው ለስራ የተሰጠውን የትራፊክ ቁጥጥር የደንብ ልብሱን በመደበኛነት በተጠቀሰው ቦታ ጊዜና ሰዓት ብቻ በመልበስ የትራፊክ ቁጥጥር ተግባሩን የሚያከናውን ሲሆን ከተጠቀሱት ጊዜያት፤ ሰአታት እና ቦታዎች በስተቀር የደንብ ልብሱን ለብሶ መገኘት ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡ የትራፊክ ተቆጣጣሪው በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ለቁጥጥር ስራው የሚሠጡትን የደንብ ልብሶች በተገቢው ሁኔታ ንጽህናቸውን በመጠበቅና በመያዝ በመደበኛው የስራ ቦታና ጊዜ ብቻ ለብሶ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡በባለስልጣኑ በትራፊክ ቁጥጥር ስራ ላይ የተመደበ የትራፊክ ተቆጣጣሪ

በመደበኛነት ለቁጥጥር ስራ ሳይት ወይም የስራ ቦታ እና ሌሎች ቦታዎች ላይ የትራፊክ ተቆጣጣሪ መሆኑን የሚያሳይ በባለስልጣኑ መሃተምና ፊርማ የተደገፈ ማንነቱን የሚገልጽ ባጅ ለተገልጋዮች በሚታይ መልኩ በማድረግ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡

### 3.31.3 የሞተር ብስክሌት አጠቃቀም

በባለስልጣኑ ቅድሚያ የሞተር ብስክሌ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚገባቸው የየቁጥጥር ዘርፉን የሚመራ የማዕከል ወይም የቅ/ጽ/ቤት ዳይሬክተሮች(መኪና የማይመደብላቸው ከሆነ) ፣ የትራፊክ ቁጥጥር ቡድን መሪ ፣ የትራፊክ ቁጥጥር ቡድን አስተባባሪዎች በቅደም ተከተላቸው እንዲሁም የኩነት ፈቃድና ቁጥጥር ቡድን መሪና ባለሙያዎች ይሆናል፡፡ በትራፊክ ቁጥጥር ስራ ተሰማርተው ሞተር የሚጠቀሙ ተቆጣጣሪዎች ከባለስልጣኑ የተረከበውን ሞተር ብስክሌት በአግባቡ በመያዝ መጠቀም አለበት፡፡ሞተር ብስክሌቱን የትራፊክ ቁጥጥር ስራ እንደ ምልክት የሚያገለግል እንደመሆኑ መጠን ከባለስልጣኑ የትራፊክ ቁጥጥር ስራ ባልደረቦች በስተቀር ለሌላ 3ኛ ወገን ተላልፎ ሊሰጥ አይችልም፡፡ሞተር ብስክሌት በሚጠቀምበት ወቅት በማኛውም ሁኔታ ቢሆን የባለስልጣኑ ሎን ያለበት አንፀባራቂ ሳይለብስ እና አሽከርካሪው ወይም አብሮ የተሳፈረው ሰው የጭንቅላት መከላከያ ቆብ ሳያደርግ ሞተር ብስክሌት በየትኛውም መንገድ ላይ ማሽከርከር የለበትም፡፡ በሞተር ብስኬሌቱ ላይ የባለስልጣኑ ባልደረባ ያልሆኑ ግለሰቦችን መጫን አይፈቀድለትም፡፡የሞተር ብስክሌት ተጠቃሚ የሆኑ ሠራተኞች የተረከቡትን ሞተር ብስክሌት ሊነጠቁ የሚችሉት በዲሲፐሊን ወይም ወይም በሌላ ምክንያት የስራ መደባቸውን ሲለቁ ወይም ሲነሱ ወይም በዚህ ማንዋል የተቀመጡ ኃላፊነቶችን በሚቃረን ተግባር ተሳትፈው ሲገኙ ይሆናል፡፡

## 3.32 ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን ቅንጅታዊ የትራፊክ ቁጥጥር ማድረግ

### 3.32.1 ከአጎራባች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ከማዕከል ትራፊክ ቁጥጥር ጋር በመሆን ቁጥጥር ማድረግ

ሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሚዋሰኑባቸው ቦታዎች በመቀናጀት የትራፊክ ቁጥጥር ስራዎች ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡የማእከል ትራፊክ ቁጥጥር ቡድን በራሱ በሚያወጣው የድጋፍ መርሀ ግብር በተቸማሪ የተለየ እቅድ በማዘጋጀት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከማእከል የትራፊክ ቁጥጥር ቡድን ጋር ቅንጅታዊ የትራፊክ ቁጥጥር ስራዎችን ይሰራሉ፡፡

### 3.32.2 ከአዲስ አበባ ከተማ ትራፊክ ፖሊስ ጋር በመሆን ቅንጅታዊ የስምሪት ቁጥጥር ማድረግ

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ መንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህችን ለማስከበር ስልጣን ከተሰጣቸው ተቋማት መካከል የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ አንዱ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ከትራፊክ ፖሊስ ጋር ቅንጅታዊ የትራፊክ ቁጥጥር ስራ ከማድረግ ባለፈ ህገ ወጥ ተግባራት ፈጽመው የሚሰወሩ አሽከርካሪዎችና ባለንበረቶችን አድኖ ለመያዝ ከፖሊስ ጋር በቅንጅት መስራትን ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሚቆጣጠሩዋቸው ክፍለ ከተሞች የፖሊስና የትራፊክ ፖሊስ ዲቪዥን ጋር እንዲሁም የማዕከል ትራፊክ ቁጥጥር እና ኩነት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከማእከል የፖሊስና የትራፊክ ፖሊስ ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት መፍጠር ይጠበቅበታል፡፡

### 3.32.3 ከአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ባለስልጣን ጋር በመሆን ቅንጅታዊ የትራፊክ ቁጥጥር ማድረግ

የአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት በከተማው ውስጥ የደንብ ጥሰትና ህገ ወጥ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር የአስፈጻሚነት ስልጣን የተሰጠው ተቋም ከመሆኑ አንጻር በአንዳንድ የእግረኛ የተሽከርካሪ መንገዶች ላይ መንገድን ከታለመለት አላማ ውጭ ጥቅም ላይ የሚያውሉ ሰዎች ላይ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ ከደንብ ማስከበር ጋር በቅንጅት መስራትን ስለሚጠይቅ ሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሚመሩዋቸው ክፍለ ከተሞች ከሚገኙ የደንብ መስከበር ጽ/ቤቶች ጋር እንዲሁም ማእከል የትራፊክ ቁጥጥርና ኩነት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከማእከል የደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ጋር በመቀናጀት በጋራ ህጋዊ የቅጣት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋሉ፡፡

### 3.32.4 ከትራንስፖርት ቢሮ ስምሪት ቁጥጥር ጋር በቅንጅት ቁጥጥር ማድረግ

የትራንስፖርት ቢሮ የትራንስፖርት ስምሪት ተቆጣጣሪዎች በተለይም በብዙሀን ትራንስፖርት ተርሚናሎች አካባቢ ሊፈጠር የሚችለውን የትራፊክ መጨናነቅ ለመቀነስ ቅንጅታዊ ስራ መስራት ይጠይቃል፡፡ታክሲ ተርሚናሎችም ሆነ ብዙሀን ትራንስፖርተ ፌርማታዎች በሚመረጡበት ወቀት የትራፊክ እንቅስቃሴውን በማያውክ መልኩ እንዲመረጥ መደረግ አለበት፡፡የትራፊክ ቁጥጥር ቡድን በየጊዜው በሚያደርገው የትራፊክ ቁጥጥር ስራ ትኩረት ከሚያደርግባቸው እና መረጃ ከሚይዝባቸው ጉዳዮች አንዱ የትራፊክ ፍሰት የሚያሰናክሉ ተርሚናሎች እና ፌርማታዎችን በመለየት ሪፖርት ማቅረብ ይሆናል፡፡በታክሲ ትራንስፖርት አገልግሎት በተሰማሩ አሽከርካሪዎች ሚፈፀሙ ደንብ መተላለፍ ጥፋቶች አሽከርካሪው ባለመገኘቱ ወይም ፈቃደኛ ባለመሆኑ ለማስፈፀም ባስቸገረ ጊዜ ከትራንስፖርት ስምሪት ቁጥጥር ባለሙዎች ጋር በመቀናጀት ማስፈፀም ችግሩን በቀላሉ ለመፍታት እንደ አንድ አማራጭ ሊወሰድ እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል፡፡

### 3.32.5 ከአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ጋር በቅንጅት መስራት

ለትራፊክ ቁጥጥር ስራ አጋዥ ከሆኑ ባለድርሻ ተቋማት መካከል የአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን አንዱ ነው፡፡ባለስልጣኑ በከተማው ውስጥ ተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች መረጃ በእጁ ስለሚገኝ የትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋት በመፈፀም ያመለጡ አሽከርካሪዎችን መረጃ በቀላሉ ማግኘት እና ተሽከርካሪውን ባለንብረት አድራሻ በመውሰድና በማስጠራት አሽከርካሪውን እንዲያቀርብ በማድረግ ደንብ መተላለፍ ጥፋቱን ማስፈፀም ይቻላል፡፡ከዚህም ባለፈ የደንብ መተላለፍ ጥፋት ፈፅመው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ የተያዘባቸው ደንብ ተላላፊዎች በተለያየ ምክንያት በወቅቱ በመቅረብ ግዴታቸውን ተወጥተው ተያዘውን መረጃ ለመውሰድ ቢቀሩ ግዴታቸውን ሳይወጡ ቦሎ እንዳያድሱ በማድረግ ማስፈፀም ይገባል፡፡

# ክፍል አምስት

# 4. የዲጅታል የትራፊክ ቅጣት ማስፈፀሚያ ሲስተም አሰራር

## 4.1 ቅጣት በዲጅታል የትራፊክ ቅጣት ማስፈፀሚያ ሲስተም ብቻ ስለማስፈጸም

1. ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር ማንኛውም ተቆጣጣሪ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ህጎችን በመተላለፍ የሚጣሉ ቅጣቶችን ሁሉ በዲጅታል የትራፊክ ቅጣት ማስፈጸሚያ ሲስተም መሠረት ብቻ እንዲፈጸም ማድረግ አለበት፡፡
2. በዲጅታል የትራፊክ ቅጣት ማስፈፀሚያ ሲስተም ቅጣት እንዲተላለፍ ከተደረገ በኃላ ማንኛውም ማስተካከያ ሊደረግ የሚችለው ቅጣቱን ያስተላለፈው ትራፊክ ተቆጣጣሪ ቅ/ጽ/ቤት ጉዳዩ አሳማኝ መሆኑን በማረጋገጥ ማስተካከያ እንዲደረግ በመፍቀድ በደብዳቤ ሲያሳውቁ ብቻ ነው፡፡
3. በሲስተም የተላለፈ የትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋት ቅጣት መከፈል ያለበት ባለስልጣኑ ውል በገባባቸው ባንኮች በሲስተም መሆን እያለበት ከሲስተም ውጪ በቀጥታ ከባለስልጣኑ ሂሳብ ገቢ የተደረጉ የቅጣት ክፍያዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ደንብ ተላላፊው በሲስተም የተላለፈለትን ቅጣት በቅድሚያ በተዘጋጀው የክፍያ ስርዓት መሠረት በመፈፀም ከሲስተም ዉጪ ገቢ ያደረገውን ገንዘብ የባለስልጣኑን አሰራር በመከተል ተመላሽ እንዲደረግለት መጠየቅ ይችላል፡፡
4. የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 557/2016 በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃ ተግባራዊ የሚደረገው ከጥር 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ይሆናል፡፡በዚህ መሠረት ከጥር 1 ቀን 2017 ዓ.ም በፊት በትራፊክ ደንብ መተላለፍ ምክንያት ቅጣት የተጣለባቸው አሽከርካሪዎች ቅጣታቸውን የሚከፍሉት በቀድሞው ህግ መሠረት ሲሆን ያለባቸው የቅጣት ገንዘብ ከነ ወለዱ ተሰልቶ እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡

## 4.2 የትራፊክ ቅጣት ማስፈፀሚያ ሲስተም አጠቃቀም

1. ትራፊክ ተቆጣጣሪው የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ህጎችን በመተላለፍ የያዘውን ደንብ ተላላፊ በቅድሚያ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ጠይቆ በመቀበል ቁጥሩን በማስገባት መረጃው ሲመጣለት በታብሌት የመጣው መረጃ በመንጃ ፈቃዱ ላይ ካለው መረጃ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን በማረጋገጥ አስፈላጊ የቅጣት መረጃዎችን በጥንቅቄ በመሙላትና በድጋሚ የተሞላው መረጃ ትክክለኛነት በማረጋገጥ ኤሌክትሮኒክ ቅጣቱን ያስተላልፋል፡፡የተላከው የቅጣት መረጃ ለደንብ ተላላፊው እስኪደርሰው ድረስ በመጠበቅ መረጃው በትክክል መድረሱን ካረጋገጠ በኃላ ቅጣቱን በሞባይል ባንኪንግ ወድያውኑ እንዲከፍል ማድረግ ይኖርበታል፡፡
2. ደንብ ተላላፊው ቅጣቱን ወድያውኑ መክፈል የማይችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም እንዴት ፣ የትና በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መክፈል እንዳለበት መረጃ በመስጠት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይመልስለታል፡፡
3. ደንብ ተላላፊው እያሽከረከረ ያለው በቅጣት ወረቀት ከሆነና በቅጣት ወረቀቱ ላይ ያለው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ቁጥር ሲገባ ትክክለኛውን የአሽከርካሪውን መረጃ የሚያወጣ ከሆነ መረጃውን ከአሽከርካሪው የነዋሪነት ወይም የፋይዳ መታወቂያ ጋር በማመሳከር ትክክለኛ መሆኑ ከተረጋገጠ ትራፊክ

ተቆጣጣሪው ቅጣቱን በሲስተም እንዲተላለፍ ማድረግ ይችላል፡፡ነገር ግን ቅጣት በሲስተም ከተላለፈ በኃላ ለአሽከርካሪው መረጃው መድረሱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

4. ትራፊክ ተቆጣጣሪው የደንብ መተላለፍ ጥፋት ፈጽሞ በቦታው ያልተገኘ አሽከርካሪ ሲያጋጥመው ወይም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ ደንብ ተላላፊ ባጋጠመ ጊዜ የተሽከርካሪውን ሰሌዳ በመጠቀም ቅጣት ማስተላለፍ ይቻላል፡፡በዚህ ሁኔታ ቅጣት የሚያስተላልፍ ትራፊክ ተቆጣጣሪ የተሽከርካሪው ሰሌዳ በሚታይ ሁኔታ ደንብ በተላለፈበት ቦታ ሳይንቀሳቀስ የፎቶጋራፍና የቪዲዮ መረጃ መያዝ ይኖርበታል፡፡

## 4.3 ልዩ ሁኔታ

1. በዲጅታል ሲስተም የማይገኙ በተለይም የክልል የአሽከርካሪና የተሽከርካሪ መረጃዎች ሲያጋጥሙ በነባሩ አሰራር መሠረት መንጃ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ ለአንድ ጊዜ ብቻ ተቀብሎ ቅጣት እንዲፈፀም በአድራሻ ማሳወቂያ ወደ ቅ/ጽ/ቤቱ መላክ ይገባዋል፡፡መረጃው የተላከለት ቅ/ጽ/ቤት የሲስተም ባለሙያ በሲስተም ያልተገኙ መረጃዎች ለመመዝገብ በተዘጋጀው የሲስተሙ ክፍል በአዲስ መልክ በመመዝገብ ወደ ሲስተሙ እንዲገቡ በማድረግ ቅጣት እንዲከፍሉ ያደርጋል፡፡ነገር ግን በሲስተም ያልተገኘው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ከአዲስ አበባ ከተማ የተሰጠ ከሆነ ትክክለኛነቱ ከአሽተሸ ሳይረጋገጥ ወደ ሲስተም እንዲገባ ወይም እንዲመዘገብ መደረግ የለበትም፡፡
2. አስቀድሞ በተሰራ የደንብ መተላለፍ ጥፋት አማካኝነት ቅጣት በሲስተም ተጥሎበት ሳይከፍል በድጋሚ በሌላ ጥፋት የተገኘ አሽከርካሪ ቅጣቱን በሲስተም በመቅጣት ቅጣቱን ፈጽሞ እስኪመጣ ድረስ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ ይዞ ማቆየት ይገባል፣
3. ትራፊክ ተቆጣጣሪው ለደንብ ተላላፊው ቅጣት በሚያስተላልፍበት ጊዜ በተደጋጋሚ ጥፋት ምክንያት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መታገዱን የሚያሳይ መረጃ ከሲስተሙ ከታየ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን በመያዝ ለቢሮ ማስተላለፍ ይገባል፣
4. በተለያዩ የህግ ማዕቀፎች የተካተቱ የቅጣት አይነቶችና በውጪ ሀገር መንጃ ፈቃድ የሚጣል ቅጣት የሚፈፀመው በተለመደው አሰራር መሠረት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ በመጠቀም በሚዘጋጀው ቅጣት ወረቀት/ፎርም መሠረት ይሆናል፡፡
5. የደንብ መተላለፍ ጥፋት በመፈፀም በቦታው ባልተገኘ አሽከርካሪ ላይ ሰሌዳን በመጠቀም አንድ ጊዜ በትራፊክ ተቆጣጣሪ ቅጣት ከተጣለ በኃላ በሌላ ተቆጣጣሪ በተመሳሳይ ጥፋትና ቦታ ላይ ቅጣት ሊጣል አይችልም፡፡
6. እንዲቆሙ ሲጠየቁ ጥሰው የሄዱ ተሽከርካሪዎች መረጃ በሲስተሙ የተፈላጊ ተሽከርካሪ መመዝገቢያ ቦታ ላይ እንዲመዘብ ለማድረግ መረጃውን በሀርድ ኮፒ በመገልበጥ የተሽከርካሪውን አይነት፣ሰሌዳ ቁጥር፣የጥፋት አይነት፣ጥፋት የተፈፀመበት ቀን፣ልዩ ቦታና ሰዓት በመመዝገብ ለቅርብ ኃላፊው ማስተላለፍ አለበት፡፡

### 4.4 በትራፊክ ተቆጣጣሪ የተፈጸመ ስህተት ስለሚታረምበት ሁኔታ

1. በትራፊክ ተቆጣጣሪ ስህተት ምክንያት በአንድ ጥፋት ተደራራቢ ቅጣት ወይም መቀጣት ከሚገባው ውጪ በሆነ የጥፋት አይነት በሲስተም እንዲተላለፍ ተደርጎ ከተገኘ ከሲስተምና ከተቆጣጣሪው በማረጋገጥ ማስተካከያ ይደረግበታል፡፡
2. ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት በተፈጸመ ስህተት እርማት የሚደረገው ደንብ ተላላፊው የሚያቀርበውን ቅሬታ መነሻ በማድረግ የቅ/ጽ/ቤቱ የመንገድ ደህንነት ግንዛቤና ደንብ ማስከበር ዳይሬክተር ጉዳዩን በማጣራት የሚያቀርበውን የውሳኔ ሀሳብ መነሻ በማድረግ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ሲፈቅድና በደብዳቤ ሲያሳውቅ ብቻ ይሆናል፡፡
3. እያንዳንዱ በስህተት ምክንያት ከሲስተም እንዲስተካከል የተደረገ ቅጣት/ሪከርድ ማመልከቻውን ጨምሮ ውሳኔ ሀሳብና በኃላፊ የጸደቁ ሰነዶች ተደራጅተው መያዝና አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

### 4.5 የትራፊክ ግጭት/ክስተት መረጃ አያያዝ

ትራፊክ ተቆጣጠሪው በስምሪት ቦታው የትራፊክ ግጭት/ክስተት በሚያጋጥምበት ወቅት በሲስተም ለዚህ አላማ በተዘጋጀው ቦታ የደረሰውን ሁኔታ በመመዝገብ ማስተላለፍ ያለበት ሲሆን በሲስተም ያስተላለፈውን መረጃ በሀርድ ኮፒም በመመዝገብ ለቅርብ ኃላፊ ያስተላልፋል፤መያዝ ያለባቸው መረጃዎች በዚህ የአሰራር ማንዋል ላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡

### 4.6 ተፈላጊ ተሽከርካሪ ስለመመዝገብ

1. ትራፊክ ተቆጣጣሪው የቁጥጥር ተግባሩን በሚያከናውንበት ወቅት አንድ ተሽከርካሪ በተፈላጊነት በሲስተም እንዲመዘገብ መረጃውን በመያዝ ለቅ/ጽ/ቤቱ ማስተላለፍ ያለበት ተሽከርካሪው እንዲቆም ሲጠየቅ ባለመታዘዝ ጥሶ ሲሄድ ብቻ ይሆናል፡፡ትራፊክ ተቆጣጣሪው አንድን ተሽከርካሪ በተፈላጊ ዝርዝር ውስጥ እንዲመዘገብ ሲያቀርብ አስፈላጊ መረጃዎች ማለትም የተሟላ የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር፣ የጥፋት አይነት ፣ ጥፋት የተፈፀመበት ቀን ፣ ሰዓት ፣ ልዩ ቦታ ፣ የተሽከርካሪው ቀለም ፣ የሚቻል ከሆነ የፎቶ ግራፍ ወይም የቪዲዮ መረጃና ሌሎች መረጃዎች በሀርድ ኮፒ ይመዘገባል፡፡ ትራፊክ ተቆጣጣሪው በተፈላጊ ዝርዝር የመዘገባቸውን ተሽከርካሪዎች መረጃ በሀርድ ኮፒም ጭምር በመመዝገብ ለቅርብ ኃላፊው ሪፖርት በማድረግ በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ በሚዘጋጀው የተፈላጊ ተሽከርካሪዎች መመዝገቢያ ፎርም እየተመዘገበ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡
2. የማዕከል የትራፊክ ቁጥጥር እና ኩነት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በተቋም ደረጃ በተፈላጊነት የታመነባቸውን ገጭተው ያመለጡ፣ በፍ/ቤት ፣ በገቢዎች ቢሮ እንዲሁም በሌሎች ስልጣን ባላቸው አካላት እንዲያዙ ጥያቄ የቀረበባቸውን ተሽከርካሪዎች በመመዝገብና ክትትል በማድረግ እንዲያዙ ሊያደርግ ይችላል፡፡

3. በተፈላጊነት በሲስተም የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች ሲያጋጥሙ በመያዝ ቅ/ጽ/ቤቱ ለማእከል የትራፊክ ቁጥጥር እና ኩነት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ያስተላልፋል፣ዳይሬክቶሬቱ የተላለፈለትን መረጃ በሲስተም በማጣራት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በማድረግ ተሽከርካሪው ከተፈላጊነት ዝርዝር እንዲወጣ በማድረግ አጠቃላይ መረጃውን በኤክስ ኤል እየተመዘገበ እንዲያዝ ያደርጋል፣ተፈላጊ ተሽከርካሪዎችን በአግባቡ ተከታትሎ ለመያዝ የሚቻለው ትራፊክ ተቆጣጣሪው ደንብ ተላላፊዎችን በሚቀጣበት ወቅት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በማስገባት ብቻ ሳይሆን በተመሳሳይ የተሽከርካሪውን ሰሌዳም በቅጣት ሲስተም ስናስገባ በመሆኑ ቅጣት በሲስተም ሲፈፀም መንጃ ፈቃድ ቁጥር ብቻ ሳይሆን ሰሌዳም ማስገባት መዘንጋት የለበትም፡፡

## 4.7 በስህተት ወደ ባለስልጣኑ ሂሳብ ገቢ የተደረገ ገንዘብ ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ

1. የቅጣት ገንዘብ ከደንብ ተላላፊው ወደ ባለስልጣኑ የባንክ ሂሳብ እንዲተላለፍ ከተደረገ ገንዘቡ ተመላሽ የሚደረገው በዋና መ/ቤት የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ፣ ቁጥጥር እና መድን ፈንድ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እውቅና በፋይናንስ ዳይሬክቶሬት አስፈፃሚነት ይሆናል፡፡
2. የፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ከምክትል ዋና ዳይሬክተር የተመራለትን ማመልከቻው ከተቀበለ በኃላ በ3 የስራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን በማጣራት ያአግባብ ገቢ የተደረገ ገንዘብ መኖሩን ሲያረጋግጥ ለደንብ ተላላፊው ተመላሽ እንዲደረግ ለባንኩ በደብዳቤ ያሳውቃል፡፡
3. የፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ጉዳዩን ለማጣራት ከዋና መ/ቤት ወይም ከቅ/ጽ/ቤት የሚፈልጋቸው መረጃዎች ካሉ ማስቀረብ ይችላል የተጠየቁ አካላትም አፋጣኝ ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡
4. የተከፈለ የትራፊክ ቅጣት ገንዘብ ተመላሽ የሚደረገው በስህተት የተከፈለ ወይም ያላግባብ በተጣለ ቅጣት ጉዳዩ በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ታይቶ ቅጣቱ እንዲሰረዝ ውሳኔ ሲሰጥ ወይም መክፈል ከሚገባው የቅጣት መጠን በላይ ገቢ ሲደረግና በተመሳሳይ ጉዳዮች ብቻ ይሆናል፡፡

## 4.8 ቅጣት ወይም የተመዘገበ የነጥብ ሪከርድ ከሲስተም ሊሰረዝ የሚችልባቸው ሁኔታዎች

1. በትራፊክ ተቆጣጣሪዎች ስህተት ወይም በሲተም ችግር ምክንያት ፣ በአንድ ጥፋት ተደጋጋሚ ቅጣት የተመዘገበባቸው ፣ መቀጣት ከሚገባቸው የቅጣት እርከን በላይ የተቀጡ እና ያለአግባብ የነጥብ ሪከርድ የተመዘገበባቸው እንዲሁም መንጃ ፈቃድ የታገደባቸው ደንብ ተላላፊዎች መረጃ በቅ/ጽ/ቤቶች ተረጋግጦ በደብዳቤ ሲገለጽና ቅጣቱ እንዲሰረዝ በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም በመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ቁጥጥር እና መድን ፈንድ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ውሳኔ ሲሰጥ፣
2. ለደንብ ተላላፊዎች አጭር የጽሑፍ መልዕክት አለመድረሱ ከኢንፍራተክ /አፍሮ ኤስ ኤም ኤስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር / ተጣርቶ ሲረጋገጥ ወለዱ ቀሪ ሆኖ ዋናውን ቅጣት ብቻ እንዲከፍሉ በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም በመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ቁጥጥር እና መድን ፈንድ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ውሳኔ ሲሰጥ ሊሰረዝ ይችላል፣

3. ጥፋት ሳይፈጽም ከህግ አግባብ ውጪ ቅጣት የተጣለበት ደንብ ተላላፊ ስለመኖሩ ወይም የተፈፀመው ጥፋት ከሚያስቀጣው የቅጣት መጠን በማስበለጥ ቅጣት የተጣለ መሆኑ በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታው ታይቶ፣ ቅጣቱ እንዲነሳ የውሳኔ ሀሳብ ቀርቦ በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም በመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ቁጥጥር እና መድን ፈንድ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ውሳኔ ሲሰጥ፣
4. በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 557/2016 መሠረት በነጥብ ቅጣት መሰረት የተመዘገበበት ነጥብ የእግድ ጣራው ላይ ከመድረሱ በፊት የቅጣት ነጥቡን ለማስቀነስ የዕውቀትና ክህሎት ስልጠና እንዲወስድ በባለስልጣኑ ተፈቅዶለት ስልጠናውን በመውሰድ ያጠናቀቀ አሽከርካሪ፣
5. ከተፈፀሙ አንድ አመት ያለፋቸው የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች አማካኝነት የተመዘገበ የነጥብ ሪከርድ፣
6. በተፈጸመ ተደጋጋሚ ጥፋት በተመዘገበ የነጥብ ሪከርድ አማካኝነት የታገደ አሽከርከሪ የእግድ ጊዜውን በመጨረስ የተሀድሶ ስልጠናና አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን ሲያጠናቅቅ፣
7. ከላይ ከተዘረዘሩት ውጪ የሆኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ በባለስልጣኑ የበላይ አመራር ውሳኔ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

### 4.9 የማዕከል ሲስተም አድሚንስትሬተር ኃላፊነት

1. ሁሉንም የሲስተሙ ክፍሎች በበላይነት ይቆጣጠራል ፣ ያስተዳድራል ፣ በጽሁፍ ሲታዘዝ መሠረታዊ ማሻሻያዎች ያደርጋል፣
2. በጽሁፍ ሲታዘዝ ሲስተሙ ውስጥ በመግባት የማስተካከል ፣ የማረምና የማስወገድ ስራ ይሰራል፣
3. ሲስተሙ ላይ ሚና እንዲኖራቸው ለሚፈለጉ የባለስልጣኑ ባለሙያዎች በበላይ አመራር እውቅና እና ፈቃድ የመጠቀሚያ(ዩዘር )አካውንት ይሰጣል፣
4. ከሚመለከተው የስራ ክፍል እግድ እንዲነሳ አስፈላጊው ፎርማሊቲ ተሟልቶ በጽሁፍ ሲቀርብ እንዲነሳ ያደርጋል።
5. የዲጅታል ትራፊክ ቅጣት ማስፈፀሚያ ሲስተም ላይ የሚደረጉ ማናቸውም ማስተካከያዎችና እርማቶች በበላይ አመራር ሲመራለት እንዲስተካከል ያደርጋል፡፡
6. በሲስተም ላይ መደረግ ያለባቸው ማናቸውም አይነት ማሻሻያዎችና ማስተካከያዎች ወይም የመረጃ ልውውጦች በተቋሙ የበላይ አመራር ውሳኔና አመራር ሰጪነት ብቻ እንዲፈፀም ያደርጋል፣
7. የሲስተሙ ውጤታማነት የበለጠ ለማሳደግ የሲስተሙ አጠቃላይ አፈፃፀምና አሰራር በየጊዜው በመፈተሽ ወይም ከተቋሙ የበላይ አመራር የሚቀርብለትን ግብረ መልስ በመቀበል የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል።

### 4.10 የትራፊክ ቁጥጥር እና ኩነት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ኃላፊነት

1. በደንብ መተላለፍ ጥፋት ሪከርድ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እግድ ያስተናግዳል፣
2. በሲስተሙ ላይ አጠቃላይ በከተማ ደረጃ ያለውን የትራፊክ ቅጣት ሁኔታ ማየትና መከታተል ይችላል፣

3. አዳዲስ የህግ ማዕቀፎች ሲወጡ ወይም ማሻሻያ ሲደረግ በሲስተም ላይ እንዲጫኑ/እንዲጨመሩ ያደርጋል፣
4. የትራፊክ ጥፋቶችን ፣ የመንገድ ትራፊክ ክስተትን እና ቅጣቶችን ይከታተላል/የሚከታተል የሰው ኃይል ይመድባል/እንዲመደብ ያደርጋል፣
5. በደንብ መተላለፍ ጥፋትም ሆነ በሌላ ጉዳይ ተፈላጊ ተብለው የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎችን በሲስተም ላይ ያያል፣ይከታተላል እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣ከተፈላጊነት ዝርዝር እንዲወጡ ያደርጋል፣
6. በተደጋጋሚ ጥፋት ሲስተም ወይም በትራፊክ አደጋ ምክንያት የታገዱ አሽከርካሪዎችን እግድ ተከታትሎ ያስፈጽማል፣ወደ ተሀድሶ ስልጠና ይልካል ስልጠናቸውን አጠናቀው ሲመለሱ እግድ እንዲነሳ ያደርጋል፣
7. በሲስተም ያልተመዘገቡ የደንብ ተላላፊዎችን መረጃ ምዝገባ ያካሂዳል፣የምዝገባ ስህተት እንዲታረም ያደርጋል፣
8. እንዳስፈላጊነቱ የማዕከል የሲስተም አድሚኒስትሬተርን ኃላፊነት ስራ ወደ ስራክፍሉ ሲወርድ ተረክቦ ይሰራል፣

## 4.11 የቅርንጭፍ ጽ/ቤት ኃላፊነት

1. በሲስተሙ ላይ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን የቅጣት ሁኔታ ማየትና መከታተል ይችላል፣
2. የደንብ ተላላፊዎችን መረጃ መመዝገብና ወደ ሲስተም ማስገባት፣
3. ከሲስተም ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች ሲሰቀርቡ በማጣራት የውሳኔ ኃሳብ በጽሁፍ ለማዕከል ያቀርባል፣
4. የቅ/ጽ/ቤት ስራ አስኪያጆች የሲስተሙን አሰራርና አጠቃላይ አፈፃፀም በቅርብ በመከታተል ችግሮች ካጋጠሙ ወድያውኑ ይፈታሉ ወይም እንዲፈቱ ያደርጋሉ።
5. ለሲስተሙ ውጤታማነት ከማእከል የሚሰጡ መረጃዎችና አቅጣጫዎች እየተከታተሉ እንዲፈጸሙ ያደርጋሉ፣
6. በትራፊክ ተቆጣጣሪ የተፈጸመ ስህተት ወይም የተጣለ ተደራራቢ ቅጣትና ሪከርድ እንዲታረም የቀረበላቸውን ቅሬታ በአግባቡ እንዲጣራ በማድረግ የመጨረሻ ውሳኔ በመስጠት ለማዕከል ያስተላልፋል አፈፃፀሙንም ይከታተላል፡
7. የዲጅታል የትራፊክ ቅጣት ማስፈፀሚያ ሲስተም አፈፃፀም በየጊዜው በመገምገም የአፈፃፀም ሪፖርት ለማዕከል እንዲተላለፍ ያደርጋሉ፣

## 4.12 የቅርንጫፍ ሲስተም አድሚንስትሬተር ኃላፊነት

1. በሲስተም ያልተገኙ የአሽከርካሪ ወይም የተሽከርካሪ መረጃዎች ወደ በሲስተም እንዲመዘገቡ ያደርጋል፣
2. ከቅ/ጽ/ቤቱ አውቅና ውጪ በሲስተሙ ላይ ተጨማሪ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን ወይም መረጃዎችን ለሶስተኛ አካል አሳልፎ መስጠት የለበትም፣
3. የደንብ ተላላፊ ቅጣቶች ላይ ሊደረግ የሚገባውን ማንኛውም ማሻሻያ ወይም እርማት መረጃዎች በአግባቡ በማደራጀት ለውሳኔ ለቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ያቀርባል፣

4. በነጥብ ሪከርድ አማካኝነት በቅ/ጽ/ቤቱ የሚታገዱ አሽከርካሪዎችን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ተቀብሎ ይይዛል፣የእግድ ሁኔታውን ለማዕከል በደብዳቤ ያሳውቃል፣
5. የእግድ ጊዜያቸውን የጨረሱ አሽከርካሪዎች ከማዕከል በሚተላለፍለት መረጃ መሰረት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲመለስ ያደርጋል፣

### 4.13 የትራፊክ ተቆጣጣሪ ኃላፊነት

1. ቅጣት በሲስተም በሚያስተላልፍበት ወቅት ስህተት እንዳይፈጠር ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያለበት ሲሆን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስህተት ከተፈጠረ ችግሩ እንዲታረም ለቅርብ ኃላፊው የተፈጠረውን ችግር አይነት ሊፈጠር የቻለበትን ምክንያት በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
2. የትራፊክ ተቆጣጣሪዎች ሲስተሙን መጠቀም ሲጀምሩ የተሰጣቸውን ታብሌት በአግባቡና በጥንቃቄ መያዝ ይጠበቅባቸዋል፣
3. በታብሌቱ ውስጥ የሚገኘውን ሲምካርድ ማውጣት፣የቅጣት አፕሊኬሽን ማውጣት፣ ታብሌቱን ፎርማት ማድረግ ፣ ማንኛውንም ማህበራዊ ሚዲያ መጠቀም ፣ ዳታውን ከቅጣት አላማ ውጪ ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠትና ለሌላ አላማ መዋል እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶች መፈፀም የለባቸውም፣
4. ከመጠቀሚያ ታብሌቱ ጋር በተያያዘ የሚያጋጥሙ ማናቸውም ችግሮች ወድያውኑ ለተቋሙ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡
5. የትራፊክ ክስተቶችን በምስል የተደገፈ መረጃ በመያዝ ያስተላልፋል፣ ክስተቱን በመቆጣጠር መንገዱ ለትራፊክ ክፍት እንዲሆን ያደርጋል፣
6. ደንብ ተላላፊው በሌለበት ኤሌክትሮኒክስት የትራፊክ ቅጣት ሲያስተላልፍ የፎቶግራፍና የቪዲዮ ማስረጃ ቀርፆ ይይዛል፣በቅርብ ኃላፊ ሲጠየቅ ያቀርባል፣



Addis Ababa Traffic Management Authority

## ክፍል ስድስት

# 5. የጥፋት ሪከርድ ስለሚያዝበት ሁኔታ እና የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ስለማገድ

## 5.1 የጥፋት ሪከርድ ስለመያዝ

1. ማንኛውም አሽከርካሪ በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 557/2016 ሠንጠረዥ "ለ" የተቀመጡ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋቶች ፈፅሞ ሲገኝ ከገንዘብ ቅጣት በተጨማሪ የጥፋት ሪከርድ ይመዘገብበታል፡፡የሚመዘገበው የጥፋት ሪከርድ በሲስተም መሠረት የሚከናወን ቢሆንም የማዕከል የደንብ ተላላፊዎች አስተዳደር ቡድን መረጃውን በየጊዜው በኤክስ ኤል ባክ አፕ መያዝ ይኖርበታል፡፡

2. ማንኛውም አሽከርካሪ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ደንብ በመተላለፉ ምክንያት የተጣለበትን ቅጣት በወቅቱ ካልፈፀመ በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 557/2016 ተጨማሪ የገንዘብ ቅጣት እና የነጥብ ሪከርድ ይመዘገብበታል፡፡ በዚህ መሠረት ማንኛውም የደንብ መተላለፍ ጥፋት ቅጣት በ10 ቀናት ውስጥ መፈፀም ያለበት ሲሆን ከ11ኛው ቀን ጀምሮ በእያንዳንዱ ቀን 5%ወለድ ጨምሮ እንዲከፈል ይደረጋል፣የሚከፈለው ወለድ በነጠላ (Simple Interse) የወለድ ስሌት መሠረት ሲሆን ማንኛውም ቅጣት የሚስያስከፍል አመራር የዘገየ ቅጣት ሲቀርብለት በአግባቡ በማስላት ከነወለዱ ማስከፈል ይጠበቅበታል፡፡ ወለዱ በሲስተም እንዳይፈጸም ሁኔታ ካጋጠመ በቅጣት ወረቀቱ የጀርባ ክፍል መከፈል የሚገባውን የገንዘብ መጠን በመጥቀስ በማህተም አስደግፎ ለባንክ ማስተላለፍ አለበት፡፡

3. ደንብ ተላላፊው ለሁለተኛና ከዚያ በላይ ጥፋት ሲፈጽም በሚመዘገበው የጥፋት ሪከርድ መሠረት ያጠፋው ጥፋት ከሚያስቀጣው ቅጣት ላይ የጥፋት ሪከርዱ በደረሰበት ልክ ተጨማሪ ቅጣቱ እየተደመረ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

4. የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች የጥፋት ሪከርድ ባለስልጣኑ በሚያለማው የመረጃ ቋት መሠረት እንዲመዘገብ እና እንዲያዝ ይደረጋል፡፡

5. የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋት ምክንያት የሚመዘገበው ነጥብ በሪከርድነት ተመዝግቦ የሚቆየው ለአንድ ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡ይህ የአንድ ዓመት ጊዜ የሚሰላው ጥፋት ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ ሲሆን አንድ አመት ሲሞላው የተመዘገበው ነጥብ ሲስተሙ በራሱ እየሰረዘ እንዲሄድ የሚደረግ ይሆናል፡፡አንድ ዓመት ያለፋቸው ጥፋቶች በሪከርድነት ተይዘው በደንብ ተላላፊው ላይ ምንም አይነት ተፅዕኖ እንዳይኖራቸው ማድረግ ይገባል፡፡

## 5.2 የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ስለማገድ

1. የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋት ምክንያት የሚመዘገበው ነጥብ ከ14 እስከ 16 ሲደርስ ለ6 ወር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይታገዳል፡፡

2. የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋት ምክንያት የሚመዘገበው ነጥብ ከ17 እስከ 20 ሲደርስ ለ1 የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይታገዳል፡፡
3. የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋት ምክንያት የሚመዘገበው ነጥብ 21 እና በላይ ሲሆን ለ1 ዓመት ከ6 ወር አሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይታገዳል፡፡
4. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የታገደባቸው አሽከረካሪዎች የእገዳ ጊዜያቸውን ሲያጠናቅቁ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዳቸውን መልሰው ማግኘት የሚችሉት የሚሰጠውን የተሀድሶ ስልጠና እና የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጥ እንዲወስዱ ከተደረገ በኃላ ይሆናል፡፡
5. በማንኛውም የደንብ መተላለፍ ጥፋት የተቀጣ ደንብ ተላላፊ የተጣለበትን ቅጣት በ6 ወር ውስጥ ካልከፈለ የአሽከሪካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለስድስት ወር ይታገዳል። በዚህ መሠረት የሚታገዱ አሽከርካሪዎች ከእግድ በኃላ ወለድ አይታሰብባቸውም፡፡
6. አሽከርካሪው በጥፋት የተመዘገበው ነጥብ ለእግድ ከመድረሱ በፊት በአሽተሽ የሚሰጠውን የእውቀትና ክህሎት ስልጠና በመውሰድ የጥፋት ሪከርድ እንዲቀነስለት በጽሁፍ ጥያቄ ካቀረበ ስልጠናውን እንዲወስድ ተደርጎ እስከ 4 ነጥብ ሪከርድ እንዲቀነስለት ይደረጋል፡፡
7. አንድ አሽከርካሪ በተለያየ ምድብ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ኖሮት በአንደኛው ምድብ ያለው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ከታገደ በሌሎች የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በመጠቀም የእገዳ ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት ማንኛውንም ተሽከርካሪ ማሽከርከር አይፈቀድለትም፡፡
8. የትራፊክ አደጋ ደርሶ ጉዳት የደረሰው በራሱ በአሽከርካሪው ላይ ከሆነ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አይታገድም፡፡

## 5.3 የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እገዳ አፈፃፀም

1. ባለስልጣኑ የጥፋት ነጥብ ሪከርዳቸው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲታገድ የሚያበቃ ደረጃ ላይ የደረሱ አሽከርካሪዎችን ሲቀርቡ መረጃውን ከትራፊክ ቅጣት ሲስተም በማጣራት እገዳው ትክክለኛ መሆኑን ሲያረጋግጥ አሽከርካሪው ስለመታገዱ የሚገልፅ ደብዳቤ ጽፎ ይሰጠዋል፡፡
2. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲታገድ ከተደረገ በኃላ አሽከርካሪው በተለያየ ጊዜ የፈፀማቸው የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች ዝርዝር እና የተመዘገበው ነጥብ የያዘ መረጃ ለአሽከርካሪው እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡
3. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እገዳ የተፈፀመው በትራፊክ አደጋ ምክንያት በሆነ ጊዜ በባለስልጣኑ የእገዳ ማሳወቂያውን ፈቃዱን ለሰጠው አካል ካስተላለፈ በኃላ አሽከርካሪው ስለመታገዱ ማረጋገጫ ከፈቃድ ሰጪው አካል እንዲደርሰው ማድረግ እና በየጊዜው መከታተል አለበት፡፡
4. የእገዳ ማሳወቂያው የደረሰው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሰጪ አካል አሽከርካሪው የእገዳ ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት ተቀያሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዳያወጣ መረጃው ከፋይሉ ጋር እንዲያያዝ ያደርጋል፡፡

5. የእገዳ ማሳወቂያው የደረሰው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ሰጪ አካል አሽከርካሪው የእገዳ ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት በሌላ ምድብ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዳይጠቀም አስፈላጊውን ጥረት በማድረግ አሽከርካሪው በሌላ ምድብ ያወጣው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ካለው እንዲታገድ ያደርጋል፡፡

6. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እገዳ የተደረገው ማናቸውም አይነት ጥፋት በመፈፀም የሰው ህይወት እንዲያልፍ ወይም ቀላል ወይም ከባድ የአካል ጉዳት እንዲደርስ በማድረጉ ምክንያት ከሆነ እገዳው የሚፈፀመው ምርመራውን ከያዘው የፖሊስ ተቋም መረጃው በደረሰ በ7 ቀናት ውስጥ መሆን አለበት፡፡

7. እገዳ እንዲደረግ ከፖሊስ ተቋም ለባለስልጣኑ የሚላከው መረጃ ጋር ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነጥቦች ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሀ. አደጋው የደረሰበት ቀንና ሰዓት፣

ለ. አደጋው የደረሰበት አድራሻ ክፍለ ከተማ፣ወረዳ፣ልዩቦታ

ሐ. አደጋውን ያደረሰው አሽከርካሪ ሙሉ ስምና አድራሻ፣እድሜ ፆታ

መ. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፣የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር

ሠ. ተጎጅው የሚታወቅ ከሆነ የተጎጂው ስምና አድራሻ፣ፆታ፣እድሜ

ረ. የጉዳቱን መጠን የሚገልፅ የህክምና ማስረጃ

## 5.4 የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እገዳ መቆጠር የሚጀምርበት ጊዜ

1. በነጥብ የጥፋት ሪከርድ ምክንያት የደንብ ተላላፊው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እገዳ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው አሽከርካሪው ስለመታገዱ በሲስተም ከታወቀበትና መንጃ ፈቃዱ በተቆጣጣሪ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

2. እገዳው የሚፈፀመው ማናቸውንም ጥፋት ፈፅመው የሰው ህይወት እንዲያልፍ ወይም ቀላል ወይም ከባድ የአካል ጉዳት እንዲደርስ በማድረጋቸው ከሆነ የእገዳ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው አደጋው ከደረሰበት ቀን ወይም አጥፊው ከተያዘበት ወይም ከታወቀበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

3. የትራፊክ አደጋ አድርሰው በሰው አካል ላይ ጉዳት ያደረሱ አሽከርከርካሪዎች የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 557/2016 ላይ በተቀመጠው መሠረት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዳቸው የሚታገደው ከጥር 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ በደረሰ የትራፊክ አደጋው ለደረሰ ጉዳት

ነው፡፡ከጥር 1 ቀን 2017 ዓ.ም በፊት በደረሱ የትራፊክ አደጋዎች ምክንያት ለደረሰ ጉዳት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሚታገደው በነባሩ አሰራር በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 395/2009 መሠረት ይሆናል፡፡

4. ማንኛውም አሽከርካሪ በትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋ ምክንያት በዲጂታል የቅጣት ማስተላለፊያ ሲስተም አማካኝነት በስልኩ ኤሌክትሮኒክስ መልዕክት ተልኮለት ለደንብ ተላላፊው መልዕክቱ የደረሰው ያለ ወለድ መክፈል ከሚችልበት ጊዜ በኃላ መሆኑ ከተረጋገጠ ወለዱ ከሲስተም ተሰርዞ ቅጣቱን ካወቀበት ቀን ጀምሮ አስር ቀን እስኪሞላው ድረስ ያለወለድ እንዲከፍል የሚደረግ ሲሆን አስር ቀን ካለፈው ወለዱን ጨምሮ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## 5.5 የእውቀትና ክህሎት ስልጠና ስለመውሰድ

1. በነጥብ አያያዝ ስርዓት መሠረት የተመዘገበበት ነጥብ ለእግድ የሚያበቃው ጣራ ላይ ደርሶ የታገደ አሽከርካሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲመለስለት የእውቀትና ክህሎት ስልጠና የወሰደበትን ማረጋገጫ ይዞ መገኘት ይኖርበታል፡፡የእውቀትና ክህሎት ስልጠና ይዘትና የሚፈጀው ጊዜ የመንገድ ደህንነት እና መድን ፈንድ አገልግሎት ወይም ባለስልጣኑ ከአሽተሽ ጋር በጋራ በሚያዘጋጁት የስልጠና ማንዋል የሚወሰን ይሆናል፡፡

2. የእግድ ጊዜ መጠናቀቂያው ላይ የተደረሰን አሽከርካሪ ባለስልጣኑ የትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች አስተዳደር ቡድን መሠረት ባለስልጣኑ ባዘጋጀውና የዚህ ማንዋል አካል በተደረገው ቅጽ መሠረት ለእውቀትና ክህሎት ስልጠና ወደ አሽተሽ ያስተላልፋል፡፡

## 5.6 የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እገዳ ጊዜያቸውን ስላጠናቀቁ አሽከርካሪዎች

1. የእገዳ ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ ደንብ ተላላፊዎች እገዳው ሲከናወን የተሰጣቸውን ደብዳቤ፣ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጥ የተሀድሶ ስልጠና ስለመከታተላቸው የሚያሳይ ማስረጃ ይዘው በባለስልጣኑ በመቅረብ እገዳው እንዲነሳላቸው መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ባለስልጣኑ የእገዳ ይነሳልኝ ጥያቄ ሲቀርብለት አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ እና የተሀድሶ ስልጠና ወስዶ በማጠናቀቅ የተሰጠውን የንድፈ ሀሳብና የተግባር ፈተና ማለፉን የሚገልጽ መረጃ ከአሽተሽ ሲቀርብለት እገዳው እንዲነሳ ፈቃድ ለሚሰጠው አካል በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

2. እገዳ የተደረገው በተደጋጋሚ በተፈፀመ የደንብ መተላለፍ በተመዘገበ የጥፋት ሪከርድ ከሆነ ለእገዳ ያበቃው የመጨረሻው ጥፋት የገንዘብ ቅጣት ሳይጣልበት እንዲመለስለት ይደረጋል፡፡

3. በነጥብ ሪከርድ ምክንያት ታግዶ የቆየ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለያዘው ተቆጣጣሪ መስሪያቤት ከባለስልጣኑ በሚፃፍ ደብዳቤ ብቻ እንዲመለስለት ይደረጋል፡፡

4. በአገድ ላይ ያሉ አሽከርካሪዎች የእግድ ጊዜያቸውን ከማጠናቀቃቸው በፊት ሲያሽከረክሩ ከተገኙ ከዚህ በፊት ለእግድ ካበቃቸው የጥፋት ነጥብ በእግድ ላይ እያሉ በማሽከርከራቸው ሊመዘገብ የሚገባው የጥፋት ነጥብ እንዲደመርና ቅጣት እንዲጣልባቸው ይደረጋል፡፡

5. መታገዳቸውን ሳያውቁ በቅጣት ወረቀት እያሽከረከሩ እያለ በሌላ የደንብ መተላለፍ ጥፋት ተይዘው ሰሌዳቸው የተፈታባቸው አሽከርካሪዎች አስፈላጊው መረጃ ቅጣቱን ከጣለው የትራፊክ ተቆጣጣሪ መስሪያቤት ሲተላለፍ ከሲስተም ውጪ እንዲከፍሉ ተደርጎ ሰሌዳቸው እንዲለቀቅላቸው ይደረጋል፡፡

6. የጠፋ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምትክ ለማግኘት ከእግድ ነፃ ማስረጃ ለመውሰድ የቀረቡ አሽከርካሪዎች መረጃቸው እግድ የሚያሳይ ከሆነ የእግድ ማጣሪያ ከተደረገ በኃላ መታገዱ ሲረጋገጥ የእገዳ ጊዜው የሚጀመረው ከባለስልጣኑ ቀርቦ ስለመታገዱ ካወቀበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

### 5.7 የእገዳ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሊመለስ ስለሚችልባቸው ሁኔታዎች

1. ስልጣን ያለው አካል ጉዳዩን በቅሬታ አይቶ እገዳው እንዲነሳ ትዕዛዝ ሲሰጥ፣
2. አግባብ ያለው ፍ/ቤት ጉዳዩን በማየት አሽከርካሪውን ጥፋተኛ አይደለም በማለት በነፃ ሲያሰናብት
3. አቃቢ ህግ አሽከርካሪው ጥፋተኛ ባለመሆኑ አይከሰስም በማለት የፖሊስ ወይም በፍርድ ቤት የተከፈተ መዝገብ ክስ በማቋረጥ እንዲዘጋ ሲያደርግ፣
4. በደረሰው የትራፊክ አደጋ ጉዳት የደረሰው በወቅቱ ተሽከርካሪውን ሲያሽከረክር በነበረው አሽከርካሪ ላይ ከሆነ፣
5. ፖሊስ ለእግድ ያስተላለፈው መረጃ በስህተት የተላለፈ መሆኑንና ለእግድ የሚያበቃ ጥፋት አለመፈፀሙን በደብዳቤ ሲያሳውቅ፣

### 5.8 ከእግድ ነፃ ማስረጃ ስለመስጠት

1. የጠፋ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምትክ ለመውሰድ ከእግድ ነፃ ማስረጃ በባለስልጣኑ የሚሰጥ ሲሆን ማስረጃ ለመውሰድ በባለስልጣኑ የሚቀርብ አሽከርካሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ቁጥር፣ አገልግሎት ክፍያ ፣ ፋይዳ መታወቂያና ባለስልጣኑ የሚያዘጋጀውን ቅፅ ሞልቶ በማቅረብ ማስረጃውን ማግኘት ይችላል፡፡
2. ከእግድ ነፃ ማስረጃ የሚሰጥ አካል አሽከርካሪው በጥፋት ነጥብ/በሲስተም፣ የትራፊክ አደጋ በማድረስ ያልታገደ መሆኑን ወይም የደንብ መተላለፍ ጥፋት ፈፅሞ የተያዘበትን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ቅጣቱን በወቅቱ ከፍሎ ባለመውሰድ የሚፈለግ አለመሆኑን በማረጋገጥ ማስረጃውን መስጠት አለበት፡፡

3. ለአሽከርካሪው የሚሰጠው መረጃ መረጃው የተጣራበትን ቀን፣ የአሽከርካሪው ሙሉ ስም፣ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ደረጃና ቁጥር፣ ከእግድ ነፃ መሆኑን የሚገልፅ አርፍተ ነገር እንዲሁም መረጃውን ያጣራው ባለሙያ ስምና ፊርማ ያረፈበት መሆን አለበት፡፡

4. ከእግድ ነፃ ይጣራልኝ ጥያቄ ቀርቦ የአሽከርካሪው መረጃ በሚጣራበት ወቅት በሲስተም መታገዱን የሚሳይ ሆኖ በተግባር ግን አሽከርካሪው ያልታገደ መሆኑ በባለስልጣኑ የትራፊክ መቆጣጠሪያ ወይም ሲስተሙን በሚቆጣጠረው አካል ወይም በሌላ የስራ ክፍል ሲረጋገጥ ተጣርቶ ማስረጃ እንዲሰጥ የሚደረግ ከሆነ ማስረጃውን የሚያጣራው የስራ ክፍል ወይም ባለሙያ የአሽከርካሪውን ሙሉ ስም ፣የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ቁጥር ፣ አሽከርካሪው የፈፀማቸው ጥፋቶች ብዛት፣ የአሽከርካሪ ሪከርድ ያለበት ደረጃ እና ከእግድ ነፃ መሆን አለመሆኑን በግልፅ ሚያሳይ መሆን አለበት፡፡

## 5.9 የትራፊክ ቅጣት ሪከርድ ማስረጃ ስለመስጠት

1. ማንኛውም አሽከርካሪ የትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋት ሪከርድ ማስረጃ መጠየቅና መውሰድ ይችላል፤ የትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋት ሪከርድ ማስረጃ እንዲሰጠው የሚጠይቅ ማንኛውም አሽከርካሪ ከማመልከቻው ጋር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ኮፒ፣ፋይዳ መታወቂያ ኮፒና የአገልግሎት ክፍያ ከፍሎ መቅረብ ይኖርበታል፣

2. የትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋት ሪከርድ ማስረጃ የተጠየቀው በውጪ ሀገር ለሚኖሩ ወይም ለውጪ ሀገር ኤምፓሲዎች ከሆነ ከማመልከቻው ጋር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ኮፒ፣ ፓስፖርት ኮፒና የአገልግሎት ክፍያ ከፍሎ መቅረብ ይኖርበታል፣

3. የትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋት ሪከርድ ማስረጃ የሚሰጥ ባለሙያ አሽከርካሪው በጥፋት ነጥብ/በሲስተም፣ የትራፊክ አደጋ በማድረስ ያልታገደ መሆኑን ወይም የደንብ መተላለፍ ጥፋት ፈፅሞ የተያዘበትን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ቅጣቱን በወቅቱ ከፍሎ ባለመውሰድ የሚፈለግ አለመሆኑን በማረጋገጥ ማስረጃውን መስጠት አለበት፡፡

## 5.10 የይርጋ ጊዜ

1. ማናቸውም ደንብ ተላላፊ አሽከርካሪ ለእገዳ የሚያበቃውን የመጨረሻ ጥፋት ከፈፀመበት ቀን ጀምሮ አንድ ዓመት እስኪያልፍ ድረስ ከማሽከርከር ካልታገደ እገዳው በይርጋ ይታገዳል፡፡

2. እገዳው የሚፈፀመው ማናቸውንም ጥፋት ፈፅመው የሰው ህይወት እንዲያልፍ ወይም ቀላል ወይም ከባድ የአካል ጉዳት እንዲደርስ በማድረጋቸው ከሆነ እገዳው በይርጋ የሚታገደው የወንጀል ተጠያቂነቱ በይርጋ በሚታገድበት ጊዜ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሰባት

# 6. የቁጥጥር መረጃዎች አያያዝ፣ ሪፖርት እና ቅሬታ አቀራረብ ስነ ስርዓት

## 6.1 መረጃ አያያዝ

የትራፊክ ተቆጣጣሪው ለስራ በተሰማራበት ቀን ያከናወናቸውን የትራፊክ ቁጥጥር ስራዎች፣ የተሰማራበትን አካባቢ የትራፊክ እንቅስቃሴ ሁኔታ፣ የአደጋ ሁኔታ፣ በህግ ተላላፊዎች ላይ የተወሰደውን እርምጃ በጥፋት አይነት እና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች የያዘ መረጃ ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው ቅፅ መሠረት በአግባቡ አደራጅቶ መያዝ አለበት፡፡ በዚህ መሠረት የመዘገባቸውን እና የያዛቸውን መረጃዎች በአግባቡ በማደራጀት፣ በመተንተንና በማጠናከር በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት በየ ሳምንቱ ሪፖርት ለአስተባባሪው ያቀርባል፡፡ ማንኛዉም ተቆጣጣሪ የትራፊክ ደንብ ተላላፊዉን ሙሉ መረጃ ከቅጣት ደረሰኙ ላይ በመገልበጥ እና ከማንዋሉ ጋር በተያያዘዉ ፎርም በመሙላት በየወሩ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡ የቡድን አስተባባሪውም የቀረበለትን መረጃ በተገቢው ሁኔታ በማደራጀት ይይዛል፡፡

## 6.2 ሪፖርት ስለማቅረብ

የትራፊክ ተቆጣጣሪው ቅጣት የፈጸመባቸውን ልዩ ልዩ የቅጣት ሰነዶችና መረጃዎችን በተገቢው ሁኔታ በወቅቱ በማደራጀት ይይዛል፤ ወቅቱን ጠብቆ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፡፡ የመረጃ ልውውጥ ዋነኛ የግንኙነት ስርዓት በመሆኑ የትራፊክ ቁጥጥር ሰራተኛው ሰነዶችን፣ መረጃዎችን፣ እንዲሁም ዕለታዊ፣ ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ ሪፖርቶችን በማደራጀትና በመተንተን ይይዛል፡፡

የቡድን አስተባባሪው ከትራፊክ ቁጥጥር ሰራተኛው የደረሰውን ሪፖርት በእርከንና በጥፋት አይነት በማደራጀት በየ ሳምንቱ ለቡድን መሪው ያቀርባል፡፡ቡድን መሪው በቡድን አስተባባሪው የቀረበለትን ሪፖርት በየፈርጁ በማደራጀት በወር አንድ ጊዜ ለማዕከል የትራፊክ ቁጥጥር እና ኩነት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ሪፖርት ያደርጋል፡፡

## 6.3 የድጋፍና ክትትል ግምገማና ግብረ መልስ አሰጣጥ

## 6.4 ድጋፍና ክትትል

የማእከል ትራፊክ ቁጥጥር ባለሙያዎች በተመደቡባቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና መስመሮች ያልተቋረጠ የድጋፍና ክትትል ስራዎች ይሰራል፡፡የድጋፍ ስራው ከሌሎች ጊዜያት በተሌ በጠዋትና ማታ መርሀ ግብር ተጠናክሮ የሚሰራ ሲሆን ቢያንስ በሳምት አንድ ቀን በቼክ ሊስት የተደገፈ የክትትል ተግባራት በማከናወን ለሀላፊ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## 6.5 የግምገማና ግብረ መልስ አሰጣጥ ሂደት

በማዕከል የነወር ፣ የ3 ወር ፣ የ6ወር ፣ የ9 ወርና የነዓመት የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀትና መገምገም፤ የማስተካካያ እርምጃዎችን መውሰድና ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡

የማእከል ትራፊክ ቁጥጥር በድጋፍና ክትትል ወቅት ግኝቶች በሳይት መታረም ያለባቸውን እንዲታረሙ ከማድረግ በተጨማሪ በየወሩ ድጋፍና ክትትል ለተደረገባቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ግብረ መልስ በጽሁፍ ይሰጣል፡፡



Addis Ababa Traffic Management Authority

## 6.6 የቅሬታ አቀራረብ ስነ ስርዓት

1. የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ህጎችን በመተላለፍ የቅጣት ወረቀት ወይም የኤሌክትሮኒክስ የቅጣት ማሳወቂያ መልዕክት የደረሰው አሽከርካሪ በተጣለው ቅጣት ቅሬታ ካለው ቅጣቱን ለጣለው የትራፊክ ተቆጣጣሪ ቅ/ጽ/ቤት በ2 (ሁለት) የስራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ቅ/ጽ/ቤቶች በቅሬታ አቅራቢዎች ለቀረበው ቅሬታ በጽሁፍ ምላሽ መስጠት ያለባቸው ሲሆን በቅ/ጽ/ቤቶች ቅሬታውን አቅርቦ ምላሽ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ውሳኔውን ባወቀ በ5(አምስት) የስራ ቀናት ውስጥ ከቅ/ጽ/ቤት በጽሁፍ የተሰጠውን ምላሽ በመያዝ ቅሬታውን ለባለስልጣኑ ዋና መ/ቤት ቅሬታ አጣሪ ቡድን ማቅረብ ይችላል፡፡
3. በደንብ ተላላፊዎች የሚቀርቡ ቅሬታዎች ከቅርንጫፍ ጽ/ቤት እስከ ዋና መ/ቤት ባለው አደረጃጀት ከ10 የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ማገኘት አለባቸው፡፡
4. በአስር የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን አቅርቦ ያላሻረ ቅሬታ አቅራቢ የተጣለበትን ቅጣት በአስር የስራ ቀናት ውስጥ መክፈል አለበት፡፡
5. በባለስልጣኑ ዋና መ/ቤት የተሰጠ ውሳኔ በባለስልጣኑ ደረጃ የመጨረሻ ይሆናል፡፡
6. በተወሰደ እርምጃ የሚቀርብ ቅሬታ ባለስልጣኑ ባዘጋጀው ቅፅ መሠረት የቅሬታው መነሻ በአጭሩ በፊርማ በማስደገፍ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 6.7 የዚህ ማንዋል አካል ስለሚሆኑ ሰነዶች

ይህ የአሰራር ማንዋል በስራ ላይ ከዋለ በኃላ በተቋም ደረጃ የሚተላለፉ ሰርኩላሮችና የስራ መመሪያዎች የዚህ ማንዋል አካል ተደርገው ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

## 6.8 በኃላፊነት ስለመጠየቅ

በዚህ ማንዋል ከተዘረጋው የአሰራር ስርዓት ውጪ ተግባራትን የሚያከናውን ሰው አግባብ ባለው ህግ መሠረት ተጠያቂ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 6.9 የአሰራር ማንዋሉ ስለሚሻሻልበት ሁኔታ

ይህ አሰራር ማንዋል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በባለስልጣኑ በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 6.10 የአሰራር ማንዋሉ በስራ ላይ የሚውልበት ጊዜ

ይህ የአሰራር ማንዋል ከመጋቢት ---------ቀን 2018 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ ይውላል፡፡

Traffic Management

ከበበው ሀ.ደቅሳ ጉተማ
ዋ/ ዳይሬክተር

ከበበው ሚዴቅሳ ጉተማ
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር

አባሪዎች

ቅጽ-1

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን

____________ቅርንጫፍ/ፖሊስ መምሪያ

ለትራፊክ ተቆጣጣሪ ባለመታዘዝ የሄዱ አሽከርካሪዎች መመዝገቢያ ቅፅ

| ተ.ቁ | የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር | የተሽከርካሪው አይነት | የጥፋት አይነት | ጥፋቱ የተፈፀመበት ክ/ከተማ | ልዩ ቦታ | ሰዓት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |

ማህተም

የተቆጣጣሪው ስምና ፊርማ__________ ______________

ቅፅ-2

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን

______________ቅርንጫፍ/ፖሊስ መምሪያ

### የቅጣት ፓድ ያልተዘጋጀላቸው የቅጣት አይነቶች መቅጫ ቅፅ

የአሽከርካሪው ሙሉ ስም ________________ ጾታ______ የመንጃ ፈቃድ ቁጥር_____________ የሰሌዳ ቁጥር_______________ የጥፋት የተፈፀመበት ክ/ከተማ___________ ልዩ ቦታ____________ቀን____________ ሰዓት_________ የጥፋት አይነት_________ የቅጣት መጠን__________ በቅጣቱ የተያዘው መንጃ ፈቃድ ☐ የፊት ሰሌዳ ተፈቷል ☐ የኃላ ሰሌዳ ተፈቷል ☐

የተቆጣጣሪ ስም________________ ፊርማ _______________ቀን____________

ማህተም

የተቋሙ አድራሻ አድራሻ

ቅጽ-3

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን

___________ቅርንጫፍ/ፖሊስ መምሪያ

### የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ/ወይም ሰሌዳ መረካከቢያ ቅፅ

| ተ.ቁ | የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር | የአሽከርካሪ ስም | የመንጃ ፈቃድ ቁጥር | የተሽከርካሪው አይነት | የጥፋት አይነት | ጥፋቱ የተፈፀመበት | | | | የተቆጣጣሪ ፊርማ | የተረካቢ ስምና ፊርማ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ክ/ከተማ | ልዩ ቦታ | ቀን | ሰዓት | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |

ማህተም

የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን

Addis Ababa Traffic Management Authority

ቅጽ-4

### የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን

____________ቅርንጫፍ/ፖሊስ መምሪያ

### የትራፊክ ህግ ተላላፊዎች የአድራሻ ማሳወቂያ ቅፅ

ቀን______________________

የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር________________ የተሽከርካሪው አይነት____________የጥፋት አይነት____________

ጥፋቱ የተፈፀመበት ክ/ከተማ_________ልዩ ቦታ____________ሰዓት____________የአሽከርካሪው ስም______________

የተቆጣጣሪው ስምና ፊርማ___________ ___________________የተቋሙ አድራሻ ልዩ ቦታ______________________ስልክ ቁጥር____________________

☐ የፊት ሰሌዳ ተይዟል ☐ የኃላ ሰሌዳ ተይዟል ☐ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ተይዟል

☐ የተሽከርካሪ ጎማ ተቆልፏል ☐ ሊብሬ ተይዟል

<u>ማሳሰቢያ</u>

ይህ የአድራሻ ማሳወቂያ ሰነድ የሚያገለገለው ለ12 ሰዓታት ብቻ ነው፡፡

ማህተም

ቅጽ-5

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን

--------------------ቅርንጫፍ

## የትራፊክ ህግ ተላላፊዎች ቅሬታ ማቅረቢያ ቅፅ

ቀን------------------------------

የቅሬታ አቅራቢው ሙሉ ስም------------------------------------------የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር-------------------

እርምጃ የተወሰደበት ቦታ ------------------------ ቀን-----------------ሰዓት------------የጥፋት አይነት----------

የቅሬታው መነሻ በአጭሩ----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የሚጠይቀው መፍትሄ/ዳኝነት----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ቅሬታ አቅራቢው ፊርማ---------------------------------

ማህተም

ቅፅ-6

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን

____________ቅርንጫፍ

የዲስፒሊን እርምጃ እንዲወሰድ በትራፊክ ተቆጣጣሪው የሚቀርብ አቤቱታ ማቅረቢያ ቅፅ

ቀን____________________

የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር------------- የአሽከርካሪው ስም-----------------------------------

ጥፋቱ የተፈፀመበት ክ/ከተማ--------------------ልዩ ቦታ---------------------ሰዓት----------------

አሽከርካሪው የፈፀመው ዲሲፕሊን ግድፈት---------------------------------------------

ድርጊቱ ሲፈፀም ነበሩ እማኞች----------------------------------------------------

የቡድን አስተባባሪው አስተያየት---------------------------------------------------

የትራፊክ ቁጥጥር ቡድን መሪ ውሳኔ------------------------------------------------

የቅጣት መጠን-----------------------------------------

የተቆጣጣሪው ስምና ፊርማ-------------

ቅፅ-7

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን**
**የትራፊክ ቁጥጥር እና ኩነት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት**
**የቅርንጫፍ ጽ/ቤት የድጋፍና ክትትል ሞዴል**
**ቼክ ሊስት**

ድጋፍና ክትትል የሚደረግበት ቅርንጫፍ ☐ሰ ☐ምዕ ☐ማዕ ☐ሜ ☐ደቡ

ድጋፍና ክትትል የተደረገበት ቀን_______________ ____ ሰዓት____________ ልዩ ቦታ____________

የሱፐርቫይዘር ስም __________________፤_________________ ፤ ________________________

| ተ.ቁ | የድጋፍና ክትትል የትኩረት መስኮች | መገለጫ | የክዋኔ ደረጃ | | | የሱፐርቫይዘር ተጨማሪ ግምገማና አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ደካማ | መካከለኛ | ጠንካራ | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

የሱፐርቫይዘር ተጨማሪ አስተያየት ________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________

የማዕከል ድጋፍ የሚሹ ጉዳዮች________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________

የሱፐርቫይዘር ስምና ፊርማ ______________________________

የአስተባባሪ ስምና ፊርማ ______________________________

* የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን * Addis Ababa Traffic Management Authority

ቅጽ-8

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን
## የመንገድ ትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች የአስ/ብ/ማ ፈቃድና ሰሌዳ መረካከቢያ ፎርም

የተቆጣጣሪዉስም:______________ የፓድ ደረሰኝ ቁጥር፡ከ______________እስከ______________

| ተ.ቁ | የአሽከርካሪ ስም | ሰሌዳ ቁጥር | የመ/ፈቁጥ ር | የጥፋት አይነት | የመ/ፈቃ ድአድራሻ | ዕድሜ | ጾታ | የተረ ካቢ ስም | የተረካቢ ፊርማ | የደረሰኝ ቁጥር | ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | | | | | |
| 3 | | | | | | | | | | | |
| 4 | | | | | | | | | | | |
| 5 | | | | | | | | | | | |
| 6 | | | | | | | | | | | |
| 7 | | | | | | | | | | | |
| 8 | | | | | | | | | | | |
| 9 | | | | | | | | | | | |
| 10 | | | | | | | | | | | |

ቅጽ-9

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን
የመንገድ ትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች የአሽ/ብ/ማ/ ፈቃድና ሰሌዳ መረካከቢያ ፎርም
የቡድን አስተባባሪ ስም:_______________

| ተ.ቁ | የአሽከርካሪ ስም | ሰሌዳ ቁጥር | የመ/ፈ ቁጥር | የጥፋት አይነት | የመ/ፈ.ቃድ አድራሻ | ዕድሜ | ጾታ | የተቆ ጣጣሪ ስም | የተረካቢፊ ርማ | የደረሰኝ ቁጥር | ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | | | | | |
| 3 | | | | | | | | | | | |
| 4 | | | | | | | | | | | |
| 5 | | | | | | | | | | | |
| 6 | | | | | | | | | | | |
| 7 | | | | | | | | | | | |
| 8 | | | | | | | | | | | |
| 9 | | | | | | | | | | | |
| 10 | | | | | | | | | | | |

ቅጽ-10

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን
የመንገድ ትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች የአሽ/ብ/ማ/ፈ.ቃድና ሰሌዳ መረካከቢያፎርም
የሳይት አስተባባሪ ስም:___________________

| ተ.ቁ | የአሽከርካሪ ስም | ሰሌዳ ቁጥር | የመ/ፈ ቁጥር | የጥፋት አይነት | የመ/ፈ.ቃድ አድራሻ | ዕድሜ | ጾታ | የተቆጣ ጣሪ ስም | የተረካቢ ፊርማ | የደረሰኝ ቁጥር | ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | | | | | |
| 3 | | | | | | | | | | | |
| 4 | | | | | | | | | | | |
| 5 | | | | | | | | | | | |
| 6 | | | | | | | | | | | |
| 7 | | | | | | | | | | | |
| 8 | | | | | | | | | | | |
| 9 | | | | | | | | | | | |
| 10 | | | | | | | | | | | |

ቅጽ-11

## በአዲስ አበባ ከተማ ትራፊክ ማኔጅምንት ባለስልጣን

## በደንብ መተላለፍ ጥፋት የተያዘ አሽ/ብቃ/ማረ/ፈቃ ወይም ሰሌዳ ለባለቤቱ ማስረከቢያ ቅፅ

| ተ.ቁ | የደንብ ተላላፊው ስም | ሰሌዳ ቁጥር | የመ/ፈ ቁጥር | የተረካቢው ስም | ጾታ | የፊርማ | የተመለሰበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | |
| 3 | | | | | | | |
| 4 | | | | | | | |
| 5 | | | | | | | |
| 6 | | | | | | | |
| 7 | | | | | | | |
| 8 | | | | | | | |
| 9 | | | | | | | |
| 10 | | | | | | | |

ቀን_______________

ቅጽ-12

በአዲስ አበባ ከተማ ትራፊክ ማኔጅምንት ባለስልጣን

ለተሃድሶ ስልጠና መላኪያ ፎርም

በአዲስ አበባ ከተማ አሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን
የአሽከርካሪ ተቋማት ብቃት ማረጋገጥ ፈቃድ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡-የተሀድሶ ስልጠናን ይመለከታል፣

1. የአሽከርካሪው ሙሉ ስም_______________________
2. የመንጃ ፈቃድ ቁጥር_________________________
3. የእግድ ጊዜ_________________
4. እርከን_________________

በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 557/2016 መሰረት ለተሀድሶ ስልጠና በእናንተ በኩል ወደ ማሰልጠኛ ተቋማት እንዲላኩ እንጠይቃለን ፡፡

ከሰላምታ ጋር



የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን
Addis Ababa Traffic Management Authority

ቀን_______________

ቅጽ-13

የአዲስ አበባ ከተማ ትራፊክ ማኔጅምንት ባለስልጣን

የአሽከርካሪ የትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋት ሪከርድ መግለጫ

ፎርም

ለ አሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

_________________ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡መረጃ ስለመስጠት

በቀን ___________ዓ.ም በቁጥር ቦ/አሽ/ብ/ማ/70/13 በተጻፈ ደብዳቤ ጊዜያዊ መንጃ ፈቃድ ያላቸው አሽከርካሪዎች የእድሳት ጊዜያቸው የደረሰ በመሆኑ መንጃ ፍቃዳቸው ከመታደሱ በፊት የትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋት ሪከርድ ተጣርቶ መረጃ እንዲላክ ተጠይቋል፡፡ በዚህ መሠረት አሽከርካሪው የትራፊክ አደጋ በማድረስ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያልታገደ ሲሆን በሲስተም የተመዘገበው የአሽከርካሪው የትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋት ሪከርድ ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ የተቀመጠው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

| ተ.ቁ | የአሽከርካሪው ስም | የመንጃ ፍቃድ ቁጥር | የቅጣት ሪከርድ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | |

ከሰላምታ ጋር

ቅጽ-14

## የአዲስ አበባ ከተማ ትራፊክ ማኔጅምንት ባለስልጣን

## ከእግድ ነፃ ማስረጃ ፎርም

ለ አሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን
_______________ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡መረጃ ስለመስጠት

አቶ/ወሪት/ወ/ሮ _________________የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ቁጥር_______________

ጠፍቶብኛል ብለዉ በትራፊክ ቅጣት መቀበያ ሲስተም ላይ እግድ ወይም በከባድ የትራፊክ ቅጣት መቀጣት እና አለመቀጣታቸውን አጣርተን እንድንልክ በጠየቃችሁት ደብዳቤ መሰረት

አቶ/ወሪት/ወ/ሮ ___________የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ቁጥር_______እስከ ቀን____2016ዓ.ም ድረስ ያልታገደ መሆኑን እናሳወቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ቅጽ-15

የአዲስ አበባ ከተማ ትራፊክ ማኔጅምንት ባለስልጣን

የእግድ ማንሻ ፎርም

## ለአዲስ አበባ አሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

**አዲስ አበባ፣**

ጉዳዩ፡- **የአሽከርካሪዎች እግድ እንዲነሳ ስለመጠየቅ፣**

ተቋማችን ደንብ ቁጥር 395/2009 በአዲስ አበባ ደረጃ ተግባራዊ እያደረገ እንዳለ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም በደንብ ቁጥር 395/2009 መሰረት ከባድ የአካል ጉዳትና የሞት አደጋ የሚያደርሱ አሽከርካሪዎች በቀጥታ ወደ እግድ እንደሚገቡ እና የተሀድሶ ስልጠና እንደሚሰጣቸ ደንቡ ይደነግጋል፡፡

በዚህ መሰረት ከታች በስም ተጠቃሹ ግለሰብ የ1 አመት የእግድ ጊዜያቸውን እና የተሀድሶ ስልጠናቸውን ወስደው ያጠናቀቁ በመሆኑ በእናንተ በኩል የአሽከርካሪ በቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እግድ እንዲነሳ እንጠይቃለን፡፡

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ | የመንጃ ፈቃድ ቁጥር | እግዱ ያበቃበት ቀን | የአደጋው አይነት | የተሀድሶ ስልጠና የወሰዱበት ተቋም | የእግድ ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | | | | |

ቅጽ-16

የአዲስ አበባ ከተማ ትራፊክ ማኔጅምንት ባለስልጣን

የትራፊክ አደጋ ሪከርድ ማስረጃ ፎርም

## To Whom It May Concern

**Title: Proof for Accident Free under driving License number** ______________________________

As per the request of **Mr/Mrs.** _________________ (Passport No: ________________) whom we had issued an Ethiopian Driving License under License number Grade ____________on the date of ________________ G.C. To date, Mr/Mrs. __________________ has demonstrated a commendable commitment to responsible and safe driving practices. From the time he received his license until the time we have written this letter, there is no record of any traffic offenses or criminal convictions related to driving.

Mr/Mrs.___________________ has consistently adhered to traffic laws and regulations, demonstrating a strong commitment to responsible and safe driving practices. He/she has taken great care to ensure compliance with all driving-related laws, reflecting his/her dedication to maintaining a clean and lawful driving history.

If you have any further questions or require additional information regarding Mr/Mrs.______________ driving record, please contact our Autority by citing our letter number and date of issue. We are more than willing to provide any necessary details to support this statement.

**Sincerely**

cc: - To: Deputy Manager
To: Traffic Control Directorate
**T.M.A**